‹‹ . . . ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይሻዋልና ተነሣ፤
ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ምድረ ግብፅ ሽሽ፤
እስክነግርህም ድረስ በዚያ ኑር›› ማቴ. ፪፥፲፫

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፰ ቤተ አብርሃም
፲፩ ቃለ መጠይቅ
፲፬ የሕፃናት ዓምድ
፲፮ ትዝብት
፲፰ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ


የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችን መደገፍ እንደሚገባ ተገለጠ

· "አንድነታችን ለሃይማኖታችን" በሚል መሪ ሐሳብ ዐውደ ርእይ ተካሄደ

*በካሳሁን ለምለሙ*



የዐውደ ርእዩ ተሳታፊዎች በከፊል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮችን ለመፍታትና የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችን መደገፍ ተገቢ መሆኑ የየካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ መልአከ ሣህል ተክለ ብርሃን ደስታ ገለጡ፡፡

አስተዳዳሪው ይህን የተገለጠው በየካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ የየካ ክፍለ ከተማ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ተቋም "አንድነታችን ለሃይማኖታችን" በሚል መሪ ሐሳብ ከመስከረም ፳፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ/ም ለሁለት ቀናት በቆየው ዐውደ ርዕይ ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ባደረጉበት ወቅት ነው፡፡ ዋና አስተዳዳሪው በዕለቱ ባሰሙት ንግግር "እኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አባቶች ሀገርንና ሃይማኖትን ከሕገ ወጦች ለመጠበቅ በየሰንበት ትምህርት ቤቶች እያገለገሉ ያሉ ወጣቶችን መደገፍና ማበረታታት ግዴታችን ነው" ብለዋል፡፡"ወጣቶችም የቤተ ክርስቲያንና የሀገር ተረካቢ መሆናቸውን አውቀው በተሰማሩበት ዘርፍ ሁሉ ጠንክረው ሊሠሩ ይገባል" ሲሉም አክለዋል፡፡

አስተዳዳሪው አያይዘውም በዚህ ወቅት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያጋጠሟትን ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶችን ተቋቁማ እንድታልፍ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች አንድነታቸውን ማጠናከር እንደሚኖርባቸው ተናግረዋል፡፡

የየካ ክፍለ ከተማ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ተቋም ተቀዳሚ ምክትል ሰብሳቢ የሆኑት መምህር ግርማ ገብረ ማርያም በበኩላቸው ዐውደ ርዕይ ማዘጋጀት ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት አይነተኛ መሣሪያ መሆኑን አንሥተው "ከመቸውም ጊዜ በላይ ለቤተ ክርስቲያን አንድነትና ሰላም ሲባል የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችን አንድነትና አቅም ማጠናከር ግዴታችን ሊሆን ይገባል" ብለዋል፡፡ የየካ ደብረ ምሕረት ቅድስት ኪዳነ ምህረት መሠረተ ሕይወት ሰንበት ትምህርት ቤት ሰብሳቢ የሆኑት ቀሲስ ተስፋዬ ኃይሉ በዕለቱ ባስተላለፉት መልእክት "የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የነገዋን ቤተ ክርስቲያን ለመረከብ ኃለፊነት ከመውሰድ ባሻገር ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ ሊያውቋትና በቤቷም ጸንተው ሊኖሩ ይገባል" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ተቋም ተቀዳሚ ምክትል ሰብሳቢ ላእከ ኄራን መንክር ግርማ በበኩላቸው የተቋሙን አገልግሎትና ዓላማ ገልጠው በሀገር ቤትና በውጭ ሀገራት የሚገኙ ሰንበት ትምህርት ቤቶችን ማጠናከርና ወጥነት ያለው ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

"አንድነታችን ለሃይማኖታችን" በሚል መሪ ሐሳብ በየካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በተዘጋጀው ዐውደ ርዕይ አርባ ስድስት ሰንበት ትምህርት ቤቶች ተሳትፈው ሥራዎቻቸውን ማቅረባቸውን ከመረጃው ለመረዳት ተችሏል፡፡

# ማእከሉ ከባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ጋር በጋራ በጦርነት ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ ማድረጉን አስታወቀ

*በጋዜጣው ሪፖርተር*

በማኅበረ ቅዱሳን የባሕር ዳር ማእከል ከባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ጋር በመተባበር በጦርነት ምክንያት ከአካባቢያቸው ተፈናቅለው በተለያዩ ጊዜያዊ መጠለያዎች ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጊዜያዊ ድጋፍ ማድረጉን የማእከሉ ምክትል ሰብሳቢ አቶ የሽጥላ ኃይሉ አስታወቁ፡፡ እንደ አቶ የሽጥላ ገለጻ ማእከሉ የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ባቋቋመው የረድኤት ኮሚቴ አካል ሆኖ እያገለገለ ሲሆን ከምእመናን፣ከባለሀብቶችና ከአጥቢያዎች ተሰብስቦ በተገኘ ሀብት በጦርነት ለተፈናቀሉና ጉዳት ለደረሰባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የምግብ፣ የአልባሳትና የቁሳቁስ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡ከዚህ ቀደም ከመተከል፣ ከሰሜን ጎንደር እንዲሁም ከዋግኽምራ ዞኖች ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ማእከሉ ከተለያዩ የሰሜን ወሎ አካባቢዎች ተፈናቅለው በደቡብ ወሎ ዞን ደሴ ከተማ ጊዜያዊ መጠለያ ለሚገኙ ወገኖች ድጋፍ እያተደረገ መሆኑን ያስረዱት ምክትል ሰብሳቢ አቶ የሽጥላ ከምእመናን፣ከወረዳ ማእከላት፣ከአጥቢያዎች እንዲሁም ከአኅራባች ማእከላት በተሰበሰበ ሀብት ከዋግኽምራ አከባቢ ተፈናቅለው በባሕር ዳር ዘንዘልማ ጊዜያዊ መጠለያ ለሚገኙ ወገኖች ጭምር የማዕድ ማጋራት መርሐ ግብር እንደተካሄደ አስረድተዋል፡፡ ምክትል ሰብሳቢው አክለውም የባሕር ዳር ማእከል አሁንም ድረስ የራሱን ኮሚቴ አዋቅሮ ከዋናው ማእከል በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት በተለያየ ምክንያት የተጎዱና የተቸገሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለመርዳት እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡የሀብት አሰባሰብ ሂደቱ ተጠናክሮ በመቀጠሉም ከተለየዩ አካባቢዎች ድጋፎች እየመጡላቸው መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ ምክትል ሰብሳቢው አያይዘውም ማእከሉ በስልታዊ እቅዱ መሠረት ለምእመናን ሁሉን አቀፍ ተደራሽ ለመሆን ሲሠራ በመቆየቱ በተለይ በሰላም ጊዜ እናቶች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በጥሩ ሁኔታ እንዲመሩ የሚያደርጉ መርሐ ግብራት ሲተገበሩ መቆየታቸውን አንሥተው ባሕር ዳር ዙሪያ በሚገኙ የገጠር ቀበሌ አካባቢዎች በርካታ እናቶች በመርሐ ግብሩ ተጠቃሚ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም ማእከሉ የሚተገብራቸው መርሐ ግብራት አቅመ ደካማ እናቶችን ያገናዘበ መሆኑን ያስረዱት ምክትል ሰብሳቢው በማኅበራዊ ድጋፍ በኩልም ከስብከተ ወንጌል አገልግሎት ባሻገር ለከፋ ችግር ለተጋለጡ ገዳማትና አድባራት ከፍተኛ እገዛ እየተደረገ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ማእከሉ አዳዲስ የአብነት ትምህርት ቤቶችን ከመገንባት ጀምሮ ገዳማት ራሳቸውን በገቢ እንዲችሉ የሚያደርግ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ሲያስረክብ መቆየቱንም አክለዋል፡፡

# በብሪታኒያ ሙዚየም የሚገኙ የቅድስት ቤተ ክርስቲን ቅርሶች እንዲመለሱ ጥሪ ቀረበ

*በጋዜጣው ሪፖርተር*



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ

በበተለያየ ጊዜ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተወስደው እስካሁን ድረስ በብሪታኒያ ሙዚየም የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን ቅርሶች እንዲመለሱ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ለብሪታኒያ ሙዚዬም መስከረም 3 ቀን ፳)፲፬ ዓ/ም በጻፉት ደብዳቤ ጥሪ አቀረቡ፡፡ ቅዱስነታቸው ለብሪታኒያ ሙዚየም በጻፉት ደብዳቤ ከዚህ ቀደም ከመቅደላ ተዘርፈው በሙዚየሙ የሚገኙ ታቦታት እንዲመለሱ አሳስበው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ የሚፈጸምባቸው ንዋያተ ቅድሳት መሆናቸውንም አስገንዝበዋል፡፡ሙዚዬሙም የተዘረፉ ንዋያተ ቅድሳትን የመመለስ ሞራላዊ ኃፊነት እንዳለበትም አክለዋል፡፡ እስካሁን ድረስ በሙዚየሙ የሚገኙት ታቦታት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና በአማንያኑ ዘንድ ያላቸው ክብር ከፍተኛ መሆኑንና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸሚያ መሆናቸውን ቅዱስነታቸው በደብዳቤያቸው አስረድተው "የብሪታኒያ ሙዚየም ታቦታቱን በማይገባቸው ቦታ ማስቀመጡ ተገቢ አይደለም" ብለዋል፡፡ከቤተ ክርስቲያን የተዘረፉ ቅረሶች በፍጥነት መመለስ ለነገ የማይባል ጉዳይ መሆኑንም ሙዚየሙ አሳስበዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የተዘረፉ ቅርሶቿ እንዲመለሱላት የብሪታኒያን ሙዚየም ስትጠይቅ መቆየቷን ቅዱስነታቸው አስታውሰው ሙዚየሙ ግን ቅርሶቹን ለመመለስ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ሲገልጽ መቆየቱን እና በተካሄደው እልህ አስጨራሽ ክትትልና ጉትጎታም ከዚህ ቀደም የተወሰኑ ቅርሶችን የመለሰ ሲሆን ከዚህ በኋላም ቀሪዎቹን ለመመለስ ፈቃደኛ እንደሚሆን ያላቸውን እምነት ገልፀዋል፡፡ የተዘረፉ የቤተ ክርስቲን ቅርሶች ከበሪታኒያ ሙዚየም እንዲመለሱ ላለፉት በርካታ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ጥረት ሲያደረጉ መቆየታቸውን ቅዱስነታቸው ገልጠው በዚህ ጥረትም ሁለት ታቦታትና ሌሎች ቅርሶች የተመለሱ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡አሁን ለብሪታኒያ ሙዚየም የጻፉት ደብዳቤ ቀሪ ታቦታትና ሌሎች ቅርሶች እንዲመለሱ መሆኑን አክለዋል፡፡

ታዋቂው የእንግሊዙ ጋዜጣ ዘጋርዲያን በበኩሉ ከ ፲፶ ዓመታት በፊት በተለያየ ጊዜና ምክንያት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተዘርፈው የተወሰዱ ውድ ቅርሶች የበሪታኒያ ሙዚዬም ለባለቤቱ እንዲመልስ የሀገሪቱ ከፍተኛ ሙህራን ማሳሰባቸውን አስታውቋል፡፡ የእንግሊዝ ወታደሮች በ፲፰)፰፰ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት መቅደላ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅርሶችን በዝሆኖችና በበቅሎዎች ጭነው መውሰዳቸው የሚታወቅ ሲሆን ቅርሶቹም በብሪታኒያ ሙዚየም፣ በዩኒቨርስቲዎች እንዲሁም በግለሰቦች እጅ ይገኛሉ፡፡

# የቅዱሳት ሥዕላት ክብር ከየት ወደየት?

ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓቷን ከምትፈጽምባቸው ንዋያተ ቅድሳት መካከል ቅዱሳት ሥዕላት ዋነኞቹ ናቸው::ቅዱሳት ሥዕላት የትመጣቸው ጥናታዊ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው::የቅዱሣት ሥዕላት መሠረቱ ልዑል እግዚአብሔር ነው ‹‹እግዚአብሔርም አለ ‹ሰውን በአርአያችንና በአምሳላችን እንፍጠር›› (ዘፍ ፩÷፳፮)፤ እግዚአብሔር ሙሴን ‹‹ሁለት ኪሩቤል ከተቀጠቀጠ ወርቅ ሥራ፤ በሥርየት መክደኛውም ላይ በሁለት ወገን ታደርጋቸዋለህ::ከሥርየት መክደኛውም ጋር አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን፥ ሁለተኛውንም ኪሩብ በሌላው ወገን አድርገህ በአንድ ላይ ትሠራዋለህ፤ ሁለቱንም ኪሩብ እንዲሁ በሁለት ወገን ታደርጋቸዋለህ::. . . . (ዘፀ ፳፭÷፲፰–፲፱) በማለት እንዲሠራ ሲያዘው በሁለቱ ኪሩብ መካከል በሥርየት መክደኛው ላይ ሆኖ እንደሚያነጋግረውም ቃል ኪዳን በመግባት ጭምር ነው (ዘፀ ፳፭÷፳፪)::

በዘመነ ሐዲስም ቅዱስ ሉቃስ የእመቤታችንን የቅድስት ድንግል ማርያምን ‹‹ምስለ ፍቁር ወልዳ›› ሥዕል በመሣል ይታወቃል::ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥነ-ስቅለት በዕለተ ዓርብ እንደተሰቀለ አድርጎ ቀይ ከለሜዳ አልብሶ በመሣል ለጢባርዮስ ቄሳር ሰጥቶታል::ቅዱሳት ሥዕላት የእግዚአብሔርን፣ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን እንዲሁም የመላእክትን፣ የጻድቃን የሰማዕታትን ክብራቸውን ልዕልናቸውን እንዲሁም ቅድስናቸውን ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው መንፈሳዊ ኪነ ጥበባዊ ሥራዎች ናቸው::

እነዚህ በሸራ፣ በአብያተ ክርስቲያናት ግርግዳ፣ በእንጨት ፣ በወረቀት እና በመሳሰሉት ነገሮች ላይ ተሥለው የሚገኙ ቅዱሳት ሥዕላት ለአገልግሎት ሲውሉ ምእመናን ለጸሎት፣ ለትምህርት እና ለአምልኮ ይጠቀሙባቸዋል::የሚሣሉት ቅዱሳት ሥዕላትም የእግዚአብሔርን ፈጣሪነት የእመቤታችንን፣ የመላእክትን፣ የጻድቃን ሰማዕታትን ምልጃና ተራዳኢነት የሚያሳዩ፣ በረከትን የምናገኝባቸው የከበሩ ንዋያት ናቸው::ቅዱሳት ሥዕላቱ የእግዚአብሔርን ቸርነት የቅዱሳኑን ገድልና ተአምራት እንዲሁም የተገባላቸውን ቃል ኪዳን የሚያሳዩን ናቸውና ዘወትር በፊታቸው ቆመን እንጸልያለን፣ በአማላጅነታቸውም እንማጸናለን እንዲሁም የጸጋ ስግደት እንሰግድላቸዋለን::

ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸው ቅዱሳት ሥዕላት እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ትውፊት የተሣሉ ሲሆን የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የሚገልጡ፣ የእመቤታችንን ምልጃ የሚያሳዩ፣ የመላእክትን ተራዳኢነት፣ የቅዱሳንን ሰማዕትነት፣ ተጋድሎ እና የተሰጣቸውን ቃል ኪዳን ጭምር እንዲያሳዩ ተደርገው የሚሣሉ በመሆናቸው ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው::

ትልቅ ክብር እና ቦታ ኖሯቸው ቤተ ክርስቲያን ለአምልኮ ሥርዓት የምትጠቀምባቸው እነዚህ ቅዱሳት ሥዕላት አንዳንዴ ትውፊታዊነታቸውን ሳይጠብቁ ሲሣሉ ፣ ተሥለው ለገበያ ሲቀርቡ ማየት የተለመደ ሆኗል::ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የራሷ የአሣሣል ሥርዓት ያላት፣ ከቅዱሳት ሥዕላቱ ጋር የተያያዘ ታሪክ፣ ገድልን፣ ሰማዕትነትን እንዲሁም ቃል ኪዳንን የሚገልጹ ሆነው ሳለ ከዚያ ያፈነገጠ ሆነው ሲሣሉ ብሎም ከቤተ መቅደሱ እስከ ዐደባባይ በቤተ ክርስቲያን ስም ለአገልግሎት ሲውሉ ዝም ብሎ ማየቱ የነገን የቤተ ክርስቲያን ትውፊታዊ አሣሣል እየሸረሸረ ነውና ችል ሊባል አይገባም::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራሷ መንፈሳዊ የአሣሣል ጥበብ ያላት ስንዱ እመቤት ብትሆንም ዛሬ ዛሬ ምእመናን አምልኳቸውን በሚፈጽሙባቸው አብያተ ክርስቲያናት ሳይቀር እየሾለኩ የገቡ፤ ከቤተ

ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ፍጹም ተቃራኒ የሆኑ ቅዱሳት ሥዕላት ብዙዎች ናቸውና በትክክለኛውና ቤተ ክርስቲያን በምትቀበላቸው ቅዱሳት እንዲተኩ ከቤተ ክህነቱ ጀምሮ እስከ ምእመኑ ትልቅ ሥራ ሊሠራ ይገባል።

ትውፊታቸውን ያልጠበቁ፣ ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ያፈነገጡ፣ ከትክክለኛው ታሪክ ጋር የማይገናኙ ቅዱሳት ሥዕላት፣ እንዲሁም ከውጭ የሚገቡ ሥዕላት ከእያንዳንዱ ምእመን ቤት ጀምሮ እስከ ቤተ መቅደስ ዘልቀው መታየታቸው በጊዜ ሂደት ነባሮቹን የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት ሥዕላት እየገፉ፣ ከሰው ዓይን እና ልቡና እንዲረሱ እያደረገ መሆናቸውን ስንቶቻችን ልብ ብለነው ይሆን? በብዛት እየታተሙ ወደ ሀገራችን በመግባት በቤተ ክርስቲያን በር ላይ የሚሸጡ ሥዕላት ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ወረራ እያካሄዱ ነውና በጊዜ መንቃት ከሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጅ የሚጠበቅ ብቻ ሳይሆን ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያን ሥዕል ማሳየትም እንዲሁም ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያን ሥዕል ገዝቶም ሆነ አሠርቶ መጠቀምም ተገቢ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለአምልኮ የምንጠቀምባቸው ቅዱሳት ሥዕላት በአንዳንድ ምእመናን ቤት ውስጥ የተለየ ክብር እና ቦታ ሳይሠጣቸው እንደማንኛውም ዓለማዊ ሥዕል ወይም ፎቶ ተለጥፈው ይታያሉ።በምእመናን ቤት ብቻ ሳይሆን በሱቆች፣ በገበያ ቦታዎች እና በቡና ቤቶች ውስጥ ሳይቀር ቅዱሳን ሥዕላትን ማንጠልጠል ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ያፈነገጠ ከመሆኑም ባሻገር የእግዚአብሔርን ልዑል ባሕርይ፣ የቅዱሳንን ክብር ማቃለል ነውና እንዲህ ዓይነት ስሕተቶችን ማረም ፣ ማስተካከል፣ ማስተማር ከቤተ ክርስቲያን ልጆች ይጠበቃል።

ከክብር ቦታቸው ወርደው በየመንገዱ ላይ ተዘርግተው እና አቧራ እየጠጡ እንደ ዓለማዊ ዕቃዎች ሲሸጡ የሚታዩት የቅዱሳት ሥዕላት ገበያ የሚጀምረው ከቤተ ክርስቲያን በር ነው።ትክክለኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሥዕላት ከሌሎቹ ጋር ተቀላቅለው የሚሸጡት፣ የሚገዙትም የቤተ ክርስቲያን ልጆች ናቸውና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ተገቢውን ትምህርት መስጠት ይገባቸዋል።ከዚህም ባሻገር እንዲህ ዓይነት ሥዕላትን ከመንገድ ላይ ባለመግዛት የቤተ ክርስቲያን ልጆች የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል።

ከዚህም በተጨማሪ መዝሙራትን እንዲያጅቡ የሚደረጉ ቤተ ክርስቲያንን የማይወክሉ ሥዕላት፣ በመንፈሳውያት የተሌቭዥን መስኮቶች ሳይቀር የሚተላለፉ፣ ከድረ ገጽ ላይ የሚወርዱ ሥዕላት፣ በየመንገዱ የቤተ ክርስቲያንን መለያ ልብስ በለበሱ መነኮሳት ጭምር የሚሸጡ ሥዕላት፣ በድረ ገጽ በቤተ ክርስቲያን ስም ከጽሑፎች ጋር በግዴለሽነት የሚለጠፉ ቅዱሳት ሥዕላት የቤተ ክርስቲያንን የቅዱሳት ሥዕላት ክብር እና ትውፊት እያደበዘዙ ነውና በታየበት ቦታ ላይ ተግሣፅና ምክር አስፈላጊ ነው።

እንዲህ ዓይነቱን እና ሥር እየሰደደ የመጣውን የቤተ ክርስቲያንን ቅዱሳት ሥዕላት ክብር የሚያወርድ አሠራር ለዘለቄታው ለመቅረፍ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛዎቹና የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት የጠበቁ ቅዱሳት ሥዕላት እንዲሣሉ በማድረግ ለምእመናን ማቅረብ፣ በቅዱሳት ሥዕላትም ዙሪያ ተከታታይ ዓውደ ርዕዮችን ማሳየት እንዲሁም የዓውደ ምሕረት ትምህርቶችን በመሥጠት ትውልዱን ከተሳሳተ የቅዱሳት ሥዕላት ግንዛቤ ማላቀቅ ተገቢ ነው።ግንዛቤው ያለን የቤተ ክርስቲያን ልጆችም ብንሆን እንደ እነዚህ ያሉ የተሳሳቱ ቅዱሳት ሥዕላትን በምናይበት ጊዜ በማስተማር፣ በመገሠጽና በመምከር የልጅነት ግዴታችንን ልንወጣ ይገባል እንላለን።

# የመስቀል በዓልን ስናከብር ማክበሪያውንም እናስከብር!!

በካሣሁን ለምለሙ

የመስቀል በዓል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ በየዓመቱ መስከረም አሥራ ሰባት ቀን በመላው ኢትዮጵያና ኦርቶዶክሳውያን በስደት ባሉባቸው የውጭ ዓለማት ሁሉ በድምቀት ይከበራል፡፡ በዓሉ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች መዳን ሲል በመስቀል ላይ ውሎ የከፈለውን አባታዊ ዋጋ ለማጠየቅ እና ገቢረ መስቀሉ ከተቀበረበት የቆሻሻ ክምር ውስጥ ንግሥት ዕሌኒ ፈልጋ ያገኘችበትን ዕለትና ወቅት በማሰብ በተለያየ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ትዕይነት ታጅቦ በድምቀት የሚከበር ሃይኖማታዊ በዓል ነው፡፡የመስቀል በዓል ለምእመናን ከሚያበረክተው ሃይማኖታዊ ዕሴት በተጨማሪ ለሀገርና ለሕዝብ በቱሪዝሙ ዘርፍ እያበረከተ ያለው ድርሻ ታላቅ ነው፡፡

የሀገርን ገጽታ በበጎ ከማስተዋወቅ ባሻር በሀገራችን በቂ የቱሪዝም ፍሰት እንዲኖርና ለሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ዙሪያ አወንታዊ መልክ እንዲኖራት አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል፡፡ የመስቀል በዓል ለኢትዮጵያና ለዓለም ሕዝብ እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት ዩኒስኮ (UNESCO) የዓለም የማይዳሰስ ቅርስ አድርጎ መዝግቦታል፡፡ ይሁን እንጂ የመስቀል በዓል የሚያስገኘውን ሀገራዊና ሕዝባዊ ጥቅም ባለመረዳት ወይም ሆን ተብሎ በአንዳንድ የሀገራችን አካባቢዎች በዓሉንና የበዓሉን ማክበሪያ ቦታ ትኩረት ባለመሥጠት በዓሉን በማደብዘዝ ሕዝባዊና ሀገራዊ ፋይዳ እንዳይኖረው ጥረት እየተደረገ መሆኑ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ እየተፈጸሙ ያሉ ድርጊቶች እውነተኛ ማሳያዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ነውረኛ ድርጊቶች መካከል ደግሞ በዓሉ በነፃነትና በሰላም እንዳይከበር መከልከልን ጨምሮ ቤተ ክርስቲያን በሕጋዊነት ለበርካታ ዘመናት በባለቤትነት አስከብራ የተገለገለችባቸውን የበዓሉን ማክበሪ ቦታዎች የመንጠቅ ርምጃዎች መወሰድ ከተጀመረ በትንሹ ከሦስት ዓመታት በላይ አስቆጥሯል፡፡ይህ አስነዋሪ ድርጊት እየተፈጸመ ያለው ደግሞ ሀገርና ሕዝብ የሰጣቸውን መንግሥታዊ ሥልጣን ወደጎን ያሉና ለጥቅም ባደሩ አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣናትና በተደራጁ ሕገ ወጥ ቡድኖች አማካይነት ነው፡፡

ችግሩን ለመፍታት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የችግሩን ስፋትና ውስብስብነት ከግምት ውስጥ ያስገባ የመፍትሔ ርምጃዎችን ሁሉ ስትወስድ ቆይታለች፡፡በተለያዩ ጊዜያት ከመንግሥት ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይትና ምክክር አድርጋለች፡፡ምክክሩም በአንዳንድ ችግሮች ላይ መፍትሔ ቢያመጣም ጉዳዩ በመንግሥት እጅ በመያዙ በአብዛኛው የዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች እስካሁን ድረስ መፍትሔ ሳያገኙ ቀርተዋል፡፡ በአዲስ አበባ መስቀል ዐደባባይ የተከበረውን የ፳፻፲፬ ዓ/ም የመስቀል ደመራ በዓል ፋይዳና በዓሉ ሊሰጠው ስለሚገባው ክብር በቦታው ተገኝተን ከበዓሉ ተሳተፊዎችና የዘንድሮውን በዓል ማክበር ካልቻሉ አህጉረ ስብከት መካከል ያገኘነውን መረጃ ጭምር አጠናቅረን እንደሚከተለው አቅረበነዋል፡፡

በበዓሉ ተሳትፎ እያደረጉ ያገኘናቸው በፈረንሳይ መካነ ሕይወት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን በማኅሌት አገልግሎት እያገለገሉ ያሉት ርእሰ ደብር መንግሥቱ ዘለዓለም የመስቀል ደመራ በዓል ከሌላው ዓለም በተለየ መልኩ በሀገራችን ኢትዮጵያ በድምቀት እንደሚከበር ገልጠው "ይህም ቤተ ክርስቲያናችንን ሃይማኖታዊ ባህሏንና ዕሴቷን እስካሁን ድረስ ጠብቃ ያቆየች መሆኗን የሚያረጋግጥ ነው" ብለዋል፡፡

የመስቀል በዓል ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ እንደመሆኑ መጠን መንግሥት በአዲስ አበባ የሚገኘውን የመስቀል ዐደባባይን በጥሩ ሁኔታ ማስዋብ እንደቻለው ሁሉ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ያሉ አከራካሪ የዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎችን አስከብሮ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ለቤተ ክርስቲያንን ሊሰጥ እንደሚገባ ርእሰ ደብር መንግሥቱ ዘለዓለም አስገንዝበዋል፡፡ ከዚህ ቀደም መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በትብብር ይሠሩ እንደነበረ የጠቀሱት ርእሰ ደብር መንግሥቱ "በዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ላይ መንግሥትን ለማስወቀስ አላስፈላጊ ተግባር የሚፈጽሙ የታችኛው የመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ መንግሥት አስፈላጊውን የርምት ርምጃ በመውሰድ ችግሩን በዘላቂነት መፍታት ይጠበቅበታል" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አያይዘውም በአንዳንድ የሀገራችን አካባቢዎች የመስቀልን በዓል በየዓመቱ በሰላምና በነፃነት ለማክበር የሚቸገሩ ምእመናን መኖራቸውን መንግሥት ጠንቅቆ በማወቅ ለምእመናን አስፈላጊው የሕግ ከለላ እንዲደረግላቸው ርእሰ ደብር መንግሥቱ ዘለዓለም ከጠየቁ በኋላ ፀረ ሰላም ኃይሎችም ከእኩይ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አሳስበዋል፡፡

ሌላው የበዓሉ ተሳታፊ በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የመገናኛ ብዙኃን ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ሊቀ ማእምራን ፋንታሁን ሙጬ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው ቆይታ እንዳስታወቁት በመስቀሉ ኃይል ፀንተን ደኅንነታችንንና ሰላማችንን መጠበቅ ጠላቶቻችንንም ማሸነፍ እንዳለብን ካስረዱ በኋላ “በመስቀሉ የተፈጸመውን እርቅ አብነት አድርገን በሀገራችን እርቅና መግባባት እንዲመጣ መሥራት አለብን ምክንያቱም መስቀሉ ይህንን የማድረግ ኃይል አለውና” ብለዋል፡፡የመስቀል በዓል ምድራዊና ሰማያዊ ፋይዳ እንዳለውም አክለዋል፡፡

**የመስቀል ደመራ በዓል ከሌላው ዓለም በተለየ መልኩ በሀገራችን ኢትዮጵያ በድምቀት እንደሚከበር ገልጠው “ይህም ቤተ ክርስቲያናችንን ሃይማኖታዊ ባህሏንና ዕሴቷን እስካሁን ድረስ ጠብቃ ያቆየች መሆኗን የሚያረጋግጥ ነው”**

የመስቀል ደመራ በዓል በኢትዮጵያ መከበር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሃይማኖታዊ ትውፊቱን እንደጠበቀ እስካሁን ድረስ መቆየቱን ያነሡት ሥራ አስኪያጁ “ከዚህ በኋላም ሃይማኖታዊ ትውፊቱ እንዳይበረዝና እንዳይከለስ ቤተ ክርስቲያናችን ትውልዱን በተገቢ መንገድ ልታስተምር ይገባል፡፡አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን በዓላት ከመንፈሳዊነታቸው ወጥተው ከመብልና ከመጠጥ ጋር እንዲያያዙና ዓለማዊ ይዘት እንዲኖራቸው እየተረደገ ያለው እንቅስቃሴ ተገቢ አይደለም” ሲሉም ሥራ አስኪያጁ ጨምረው አስገንዝበዋል፡፡በሌላ በኩል በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች የሚገኙ የመስቀልና የጥምቀት በዓላት ማክበሪያ ቦታዎችን የመንጠቅ እንቅስቃሴዎች በመኖራቸው ቤተ ክርስቲያን ምእመናንና ወጣቶችን በማስተባበር ጥንታዊና ታሪካዊ የሆኑ ቦታዎቿን ማስከበር እንደሚጠበቅባት ሥራ አስኪያጁ ተናግረው የዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎቹ ይዞታ ሲከበር የመንግሥትን የልማት እቅድ ተከትሎ ማልማት እንደሚጠበቅም አስረድተዋል፡፡

አክለውም ቤተ ክርስቲያናችን በሀገር እንደምትመሰል በመረዳት ጥንታቷዊና ታሪካዊቷን ቤተ ክርስቲያን ማክበር የሁሉም ግዴታ ሊሆን ይገባል፡፡የመንግሥት ባለሥልጣናትም መብቷን፣ ክብሯንና ሀብቷን ጠብቀው በዓላቷ ያለምንም የፀጥታ ችግር እንዲከበር ማድረግ አለባቸው፡፡ከበዓላቱ በቱሪዝም ዘርፉ የሚገኘው ገቢ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ሕዝብና መንግሥትን የሚጠቅም በመሆኑ በዓላቱና የበዓሉ ማክበሪያ ቦታዎች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በበዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ዙሪያ ባሉ ችግሮች አህጉረ ስብከትና ሊቃነ ጳጳሳት ችግሩን ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ያስገነዘቡት ሥራ አስኪያጁ ከዚህ በኋላ ምእመናንን በማስተባበር የዐደባባይ በዓላት በሰላም፣በነፃነትና በደመቀ ሁኔታ ለማክበር አስፈላጊው ሁሉ ጥረት እንደሚደረግ ተናግረዋል፡፡

በበዓሉ ተገኝተው አባታዊ ቡራኬ የሰጡት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የመስቀል ትርጉም ሰላምና እርቅ ስለሆነ በእግዚአብሔርና በእኛ መካከል እንዲሁም በእኛና በሌሎች ወገኖቻችን መካከል ያለውን ሰላምና እርቅ መጠበቅ እንደሚገባ ያነሡ ሲሆን “ምድራችን ፍጹም ሰላም ሊሆን የሚችለው በሰዎችና በሥነ ፍጥረት መካከል ፍጹም የሆነ ሰላምና እርቅ ሲኖር ነው” ብለዋል፡፡ሕዝበ ክርስቲያኑ የሰላምና የእርቅ አምባሳደር ሆኖ እንዲሠራ ያሳሰቡት ቅዱስነታቸው የሰው ልጅ ለዚህ ተግባር በእግዚአብሔር የተሾመ መሆኑን ሊረዳ እንደሚገባም አክለዋል፡፡

በበዓሉ ዕለት ንግግር ያደረጉት የአዲስ አባባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አበቤ የመስቀል በዓል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ በየዓመቱ በድምቀት የሚከበር መሆኑን አንሥተው በዓሉ ሀገራችንን በቱሪዝሙ ዘርፍ ታዋቂና ተጠቃሚ እንድትሆን ማድረጉን ተናግረዋል፡፡በመሆኑም የመስቀል በዓል ሀገራዊ ሀብት መሆኑን አክለው አስገንዝበዋል፡፡

በውጭ ሀገራት የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳት ሀገራችን በምዕራብውያን እየደረሰባት ያለውን ጫና ለመመከት እያደረጉት ያለውን አስተዋፅኦ ከንቲባዋ አድንቀው አንድነታችንን በማጠናከር ጊዜያዊ አለመግባባቶችን ወደጎን በመተው ውጫዊ ጫናዎችን መመከት እንደሚገባም ተናግረዋል።

የባህልና ቱሪዝም ሚንስቴር ሚኒስትር ዶ/ር ጊሩት ካሣው በዕለቱ ባስተላለፉት መልእክት እንዳስታወቁት ሀገራችን ኢትዮጵያ ለሺህ ዘመናት የመስቀልን በዓል ስታከብር የቆየች መሆኗን አስረድተው የመስቀል በዓል ከሃይማኖታዊ ዕሴቱ በተጨማሪ ባህላዊ ዕሴቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መሥራት እንደሚገባ አስገንዝበዋል።አያይዘውም "የመስቀል በዓል የሰላምና የእርቅ ምልክት በመሆኑ የተጣሉትን ያስታርቃል፤ የተራራቁትንም ያቀራርባል፤ ካሉ በኋላ "መስቀል የተስፋና የመዳን ምልክት በመሆኑ በውስጣችን ያለውን ክፉ ነገር ሁሉ ጠርገን ልናወጣ ይገባል" ብለዋል።

"ከዚህ በመቀጠልም የመስቀል በዓልን የመሰሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ዕሴቶቻችን ክብራቸውን እንደጠበቁ ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ ቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን የፈጸሙትን ገድል መድገም ያስፈልጋል" ሲሉ የተናገሩት ሚንስትሯ ዶክተር ጊሩት አክለውም "በሃይማኖታዊና በባህላዊ ዕሴቶቻችን ላይ ይበልጥ ዕሴት ጨምረን ለተተኪው ትውልድ ማስረከብም ይጠበቅብናል" በማለት አስገንዝበዋል።ይህ በእንዲህ እንዳለ በርእሰ መዲናችን አዲስ አበባ እንዲህ አምሮና ደምቆ የሚታው መስቀል አደባባይ በዚሁ መልኩ እንዲሠራ ከተማ አስተዳደሩ ላበረከተው አስተዋጽኦ ክብር ይገባዋል" ሲሉ የተናገሩት ሚንስትሯ "ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ባህሎቻችንን ዕሴት ጨምሮ ለትውልድ ለማስተለላፍ ይህ የመስቀል ዐደባባይ ማሳያ ነው" ብለዋል።አክለውም ሚንስቴር መሥሪያ ቤታቸው ለሃይማኖታዊ በዓላት አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ እንደሚያደርግም አረጋግጠዋል፡

በመጨረሻም በኢትዮጵያ የዩኒስኮ ጸሓፊ የሆኑት ዶ/ር ቤዛዊት ግርማ በበኩላቸው "በሀገራችን ኢትዮጵያ የሚገኙ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ሀገራችንን በዓለም መድረክ በአድናቆት እንድትታይ እያደረጓት ይገኛሉ ካሉ በኋላ "ቅርሶቹም ይዘታቸውን እንደጠበቁ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፉ የቻሉት አባቶቻችንና እናቶቻችን ባደረጉት ተጋድሎ ነው" ብለዋል።የመስቀል ደመራ በዓል ከ፳፻፮ዓ.ም በዩኒስኮ (UNESCO) ከማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል የተመዘገበ መሆኑን ያስረዱት ዋና ጸሓፊዋ "ይህንን ድንቅ ቅርስ ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍም የሁላችንም ድርሻ ሊሆን ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

"በመቀጠልም የመስቀል በዓልን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ልጆቻችን ጠንቅቀው እንዲያውቁ ከማድረግ አኳያ የወላጆች ሚና የላቀ ነው ያሉት ዶ/ር ቤዛዊት አያይዘውም "የማንነታችንና የኩራታችን ምንጭ የሆኑት እነዚህ ቅርሶቻችን በዚህ ወቅት ለከፍተኛ አደጋ እየተጋለጡ በመሆናቸው ቅርሶቹን ከመጥፋት መታደግ የሁላችንም የሞራል ድርሻ ነው" ሲሉም በአጽንኦት አስገንዝበዋል።

አክለውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ቅርሶች ባለቤት በመሆኗ ቅርሶቿንና በዓሎቿን በመጠበቅና በማስመዝገብ በዓለም ያላትን መልካም ገጽታ የበለጠ በመገንባት በቱሪዝሙ ዘርፍ በኩል ያላትን አስተዋጽኦ ልታጎለብት እንደሚገባ ጸሓፊዋ አስረድተዋል።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ከዚህ ቀደም እንደሆነው ሁሉ የ፳፻፲፬ ዓ/ም የመስቀል ደመራ በዓል እንደማይከበር ሀገረ ስብከቱ መስከረም ፲፬ ቀን ፳፻፲፬ ዓ/ም ባወጣው መግለጫ አስታውቋል።ሀገረ ስብከቱ በዓሉ ላለመከበሩ በምክንያትነት የጠቀሰው ደግሞ "ታሪካዊና ጥንታዊ የሆነውን የመስቀልና የጥምቀት በዓላት ማክበሪያ ቦታ በከተማ አስተዳደሩ አማካይነት ስለተነጠኩ ነው" ይላል።ሀገረ ስብከቱ ያቋቋመው ኮሚቴ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግሥት አካላት ጥያቄውን በማቅረብ በሀድያ ዞን አስተዳድርና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት በኩል በጎ ምላሽ እንዳገኘ በማስረዳት በመግለጫው አንሥቶ ነገር ግን ግልጸኝነት የጎደለው የአፈጻጸም ችግር እንዳለ በማስረዳት የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ለጉዳዩ ዘላቂ መፍትሔ እስኪሰጡ ድረስ በዓለ መስቀሉ እንደማይከበርና በዚህ የተነሣም የሆሣዕና ከተማ ምእመናን በትዕግሥት እንዲጠብቁ አሳስቧል።እኛም በመስቀል በዓልና በማክበሪያ ቦታዎቹ ላይ እየተፈጸመ ያለው ሕገወጥ ድርጊት በአስቸኳይ ቁሞ ምእመናን በዓላቸውን በሰላምና በነፃነት እንዲያከብሩ መደረግ እንዳለበት የሚመለከታቸውን የመንግሥት አካላትንና ቤተ ክርስቲያንን እናሳስባለን።አምላካችን እግዚአብሔር ሀገራችንንና ቤተ ክርቲያናችንን ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠብቅልን።

# «ይህን ጉባኤ ትቼ አዲስ አበባ ብገባ እግዚአብሔር ይቀየመኛል ብዬ ከዚሁ ቀረሁ»

*በመጽሐፈ ሲራክ*

ክፍል አንድ

*በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ታች ቤት ወረዳ ቤተ ክህነት በፌጥራ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስተያን ውስጥ ላለፉት ፵፪ ዓመታት ወንበር ዘርግተው በማስተማር ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን አፍርተዋል።ዛሬም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰጠቻቸውን አደራ በመፈጸም ላይ ይገኛሉ።በአገልግሎት ዘመናቸው ሁሉ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ደምዝ ሳይቆረጥላቸው፣ ቀለብ ሳይሰፈርላቸው ቤተ ክርስቲያንን በትሩፋት ሲያገለግሉ ኖረዋል።ዛሬ ያላቸውን የሕይወት ተሞክሮ እንዲያካፍሉን እንግዳ አድርገናቸዋል እነሆ፦*

ስምዐ ጽድቅ ፦ አባታችን በቤተ አብርሃም ቤት ዓምዳችን የሕይወት ተሞክሮዎን እንዲያካፍሉን ፈቃደኛ ስለሆኑ በልዑል እግዚአብሔር ስም ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ተጋባዥ እንግዳችን፦ እኔም ለዚህ ጉዳይ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።

ስምዐ ጽድቅ፦ አባታችን ሙሉ ስምዎትን፣ የትና በስንት ዓ.ም. እንደ ተወለዱ? ቢነግሩን

ተጋባዥ እንግዳችን፦ ሙሉ ስሜ መጋቤ ስብሐት ልዑል ሲሳይ ይባላል።የተወለድኩት በሰሜን ሸዋ ዞን ሚዳ ወረዳ ውስጥ ልዩ ስሙ አገማ እምቢ በሎ በሚባል ቀበሌ በ፲፱፻፶ ዓ.ም ነው።

ስምዐ ጽድቅ፦ እስኪ ስለ ልጅነት ሕይወትዎ ይንገሩን

መጋቤ ስብሐት ልዑል ሲሳይ፦ የልጅነት ሕይወቴን ያሳለፍኩት በዚያው በተወለድኩበት አካባቢ ነው። እንደማንኛውም የገጠር ልጅ ከብት ስጠብቅ ነው ያደኩት።



መጋቤ ስብሐት ልዑል ሲሳይ

**ስምዐ ጽድቅ፦ አባታችን አብነት ት/ቤት እንዴት ገቡ? የት የት ተማሩ? እና ምን ምን ተማሩ የሚሉ ነጥቦችን ዘርዝር አድርገው ቢገልጹልን?**

**መጋቤ ስብሐት ልዑል፦** አባቴ በልጅነቴ ስለሞቱ እናቴ ከዚያው ከአደግሁበት አካባቢ ወደሚገኝ ተማሪ ቤት አስገባችኝ፡፡ ፲፰ ዓመት እስኪሆነኝ ድረስ በወቅቱ በአካባቢያችን በነበሩ ጉባኤ ቤቶች እየተዘዋወርኩ ከንባብ ጀምሮ እስከ መዝሙረ ዳዊት የቃል ትምህርቱንም እስከ መስተጋብእ እንዲሁም የሰለልኩላና መዝገበ ቅዳሴንም ተምሬአለሁ፡፡ ከዚያም መርሐ ቤቴ ማጀግና በሚባል ቦታ በዚያ ከነበሩት የዜማ መምህራን የቃል ትምህርትንና ጾመ ድጓን ተማርኩ፡፡ከዚያም ወደ ፌጥራ በመሄድ አለቃ መዘምር ከተባሉ የቅኔ መምህር ዘንድ ሁለት ዓመት ተቀምጬ ቅኔን ተምሬያለሁ፡፡

ከዚያም በኋላ ወደ ፍቼ ከተማ በመሄድ አለቃ እሸቴ ከተባሉ የዜማ መምህር እንዲሁም ወደ ኢቲሳ ተክለሃይማኖትም በመሄድ አለቃ መስፍን ከተባሉት መምህር ከእነዚህ ከሁለቱ መምህራን የቃል ትምህርትንና ጾመ ድጓውን መላልሼ ተምሬያለሁ፡፡ ወደ ጎጃም በማቅናትም በአማኑኤል ከተማ ለሦስት ዓመታት ያህል ተቀምጫለሁ፡፡ በዚያ መምህር መርዓዊ ከሚባሉ የቅኔ መምህር የቅኔ ትምህርቴን በሚገባ አደላድየ ተምሬአለሁ፡፡ በዚሁ ቦታ መምህር ሠናይ ከሚባሉ የአቋቋም መምህር አቋቋም ተማርሁ፡፡ አቋቋም እዚያ ነው በደንብ የለየሁት፡፡ ክብረ በዓል፣ መዝሙር፣ አርባዕት የተማርኩት እዚያ ነው፡፡ የአቋቋም መምህሩ የዝማሬ መዋሥዕት መምህርም ስለነበሩ ከዚያ ዝማሬ መዋሥዕት ተምሬአለሁ፡፡ በእርግጥ ለቅኔውም ለዜማውም ለስድስት ዓመታት ያህል የተቀመጥኩበትን እንጂ በዚህ በተጨማሪ ለቅኔውም፣ ለዜማውም እያልኩ ወደ ደንበጫም፣ ወደ ፍኖተ ሰላምም ተዘዋውሬለሁ፡፡

ከዚያም ወደ ጎንደር በመሄድ በአታ የአቋቋም ምስክርነት የሚሰጥበት ጉባኤ ቤት ገብቼ ለአምስት ዓመት ተቀመጥሁ፡፡ የአቋቋም ምስክር የተቀበልሁት ከዚያ ነው፡፡በዚያው ወደ ቤተ ልሔም ሄጄ ድጓ አስመሰክራለሁ ብየ አስቤ ነበር፡፡ ግን አማካሪዎቼ ይህን ሁሉ ብትማር የምትበላው በአንዱ ነው ከንቱ ባትደክም ሲሉኝ፣ እኔም አቅም ስላልነበረኝ የመማር ፍላጎቴ የሰዎቹ ምክርም ከምንም በላይ ደግሞ ድህነቴ አስሮኝ በዚሁ አብቅቷል፡፡ ያው እንግዲህ በሸዋም፣ በጎጃምም፣ በጎንደርም ተዘዋውሬ ቅዳሴ፣ ዜማ፣ ቅኔና አቋቋም ተምሬአለሁ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፦ አባታችን የትምህርት ሕይወትዎን በዚህ መልኩ ገልጸውልናል እስኪ የአገልግሎት ሕይወትዎን ደግሞ ያብራሩልን?**

**መጋቤ ስብሐት ልዑል፦** ከጎንደር አቋቋም ቤት ወጥቼ በዚያው በሰሜን ጎንደር ዞን ደልጊ ወረዳ ጉራንጌ ሚካኤል በሚባል ቤተ ክርስቲያን ለአንድ ዓመት ያህል ከዚያም ጫቅርና ማርያም ለሁለት ዓመት በድምሩ ለሦስት ዓመት ያህል አስተማርኩ፡፡ በመቀጠልም ወደ ደሴ ሄጄ በደሴ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ዓመት ያህል አስተማርኩ፡፡ ከዚያም በ፲፱፻፹፪ ዓ.ም ጥቅምት ወር ላይ ወደ መርሐ ቤቴ መጥቼ በዚህ አሁን ባለሁበት በፌጥራ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አቋቋም በማስተማር ላይ እገኛለሁ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፦ አባታችን እዚህ ቦታ ላይ ለስንት ዓመት ያህል አስተማሩ ማለት ነው?**

**መጋቤ ስብሐት ልዑል፦** ፴፬ ዓመታት መሆኑ ነው፡፡ በእርግጥ ብዙ ሰዎች ለምን አዲስ አበባ አትገባም እዚያ ብትሄድ ደህና ደሞዝ ታገኝ ነበር እያሉ ይገፋፉኝ ነበር እኔ ግን ይህን ጉባኤ ትቼ ብሔድ እግዚአብሔር ይቀየመኛል እንዲሁም ስለ ጉባኤው ፍቅር ስል እምቢ ብዬ እዚሁ ቀረሁ፡፡ ጉባኤውም እንደዚህ እንደዛሬው ሳይሳሳ ብዙ ነበረ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፦ አባታችን በተማሪ ቤት ሕይወትዎ ከገጠመዎት መልካም እና ክፉ ከሚሉት ቢያጫውቱን?**

**መጋቤ ስብሐት ልዑል፦** በተማሪ ቤት ሕይወት ብዙ ገጠመኞች ይኖራሉ ከዚያ መካከል አንዱ ክፉ ገጠመኝ

የምለውና ትልቁ ፈተና ረኃብ ነው፡፡ አስታውሳለሁ አንዴ ከረኃቡ ጽናት የተነሣ የማሽላ እንጭርጭር (በጥሬው የተቆላ) የበላሁበት ጊዜ አለ፡፡ ደረቅ በቆሎ እያመስን የበላንበት ጊዜ አለ፡፡ በተለይ ጎንደር በነበርኩ ጊዜ በዚያ ልመና እንደልብ አይገኝም ነበር፡፡ ስለዚህ ምግብ ማታ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ አንዴ ነው የሚበላው ኑሮው እንደገዳማውያን ነበር፡፡ ሙሉ ቀን ውለን ማታ ሁለት ሰዓት ላይ ውኃ በጨው በጥብጠን በዚያ እያጠቀስን ነበር የምንበላው፡፡ ያንን ጊዜ መቼም አልረሳውም፡፡ በዚያ ጊዜ በጉዳት ምክንያት እከክ ይዞኝ እጄን ሁሉ ጨርሶት እጀራ መቁረስ እስኪያቅተኝ ደርሼ ነበር፡፡ የኔ መጥፎ ገጠመኝ ይኸው ረኃቡ ነው፤ መታረዝ ነው የሚረዳኝ ሰው አልነበረምና ብዙ በመራብና በመታረዝ ተፈትኛለሁ፡፡ በእርግጥ በጊዜው ተቀጥሮ ለመሥራት ወደ ታች ወደ ቆላው ማኅበረ ሥላሴ አካባቢ የሚቀጥሩኝ አግኝቼ ነበር ነገር ግን ከነችግሬ ትምህርቴ ብማር ይሻለኛል ብዬ ቀረሁ፡፡

ጥሩ ገጠመኝ ያው እንደ ገጠመኝ ባይቆጠርም ያን በተማሪነቴ የደረሰብኝን ሁሉ መከራ የሚያስረሳውን ሕይወቴን ነው፡፡ ደጎና ሕይወት ኖርኩ የምለው በዚሁ በፌጥራ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ወንበር ከዘረጋሁ በኋላ ያለውን ሕይወት ነው፡፡ ተማሪ እያረሰልኝ ደጎና ኑሮ እኖር ነበር፡፡ በዚያ ላይ ብዙ ተማሪዎች ነበሩኝና ለአንድ መምህር ደግሞ ከምንም በላይ ሀብቶቹ ተማሪዎቹ ስለሆኑ በተማሪዎቼ እየተደሰትሁ እኖር ነበርና ያ ዘመን ለኔ መልካም ዘመን ነበር፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፦** አባታችን ከመምህርነቱ ባሻገር በምን በምን አገልግሎት ላይ ይሳተፋሉ?

**መጋቤ ስብሐት ልዑል፦** ከመምህርነቱ ባሻገር በቤተ ክርስቲያን የማኅሌት አገልግሎትም እሳተፋለሁ፡፡ መደበኛ መሪጌታ ቢኖርም ክብረ በዓል ብየ ብቻ ሳይሆን በዘወትር አገልግሎት እንደ መደበኛ አገልጋይ ነው የምሳተፈው፡፡ በሌላው ግን ማለትም ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውጭ በተለይ በፊተኛው ጊዜ በቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በመንግሥት ልማት ላይ እሳተፍ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች መንግሥት አንዳንድ የልማት ሥራዎችን ለምሳሌ በእርሻ፣ በአጨዳና በመሳሰሉት እንድንሠራ ሲጠየቅ እስከ ፪፻ የሚደርሱ ተማሪዎችን በመላክ እሳተፍ ነበር፡፡

**በእርግጥ ብዙ ሰዎች ለምን አዲስ አበባ አትገባም እዚያ ብትሄድ ደህና ደሞዝ ታገኝ ነበር እያሉ ይገፋፉኝ ነበር እኔ ግን ይህን ጉባኤ ትቼ ብሔድ እግዚአብሔር ይቀየመኛል እንዲሁም ስለ ጉባኤው ፍቅር ስል እምቢ ብዬ እዚሁ ቀረሁ፡፡**

# “የመጣውን ፈተና ሁሉ ፊት ለፊት ሳንጋፈጥ ቤተ ክርስቲያንን ለትውልድ ማስተላለፍ አንችልም”

## - የኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት የሃይማኖት አባት

### ክፍል አንድ

*በካሣሁን ለምለሙ*

*ካለፉት ሦስት ዓመታት ወዲህ በኦሮምያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር በሚገኙ አንዳንድ አካባቢዎች በቤ ተክርስቲያንና በምእመናን ላይ ፀረ ሰላም ኃይሎች ጥቃት ይፈጽሙ እንደነበረ በተለያየ ጊዜና በተለያየ መልክ መረጃውን ስናደርስ ቆይተናል፡፡ይሁን እንጂ ችግሩ ሰፊና ጥልቅ በመሆኑ የሚዲያ ፍጆታ ከመሆን በዘለለ የመጣ ለውጥ የተሻሻለ የፀጥታ ሁኔታ የለም፡፡ችግሩ ከመሻሻል ይልቅ እየሰፋና መልኩን እየቀየረ ለቤተ ክርስቲያን ውድመት ለምእመናን ሞትና መፈናቀል ምክንያት እየሆነ መጥቷል፡፡ከዚህ ቀደም ከፍተኛ የሆነ የፀረ ሰላም ኃይሎች እንቅስቃሴና እኩይ ድርጊት ተንሰራፍቶ የነበረባቸው አካባቢዎች በአሁኑ ወቅት መጠነኛ መሻሻሎች ቢታይባቸውም በምሥራቅና ምዕራብ ወለጋ አካባቢዎች እየተስተዋለ ያለው የኦርቶዶክሳውያን ሰቆቃና ቀጣይ የፀጥታ ስጋት ክልሉ ለሰላምና ለደኅንነት የሰጠው ዋጋ አናሳ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ሰላም ፈላጊ ኦርቶዶክሳውያንን የሰላም ዋጋ ስንት እንደሆነ የማያውቁ ፀረ ሰላም ኃይሎች በነፃነት እንዳያመልኩ ሲያደርጓቸውና የመኖር ነፃነታቸውን ሲነፍጓቸው ርምጃ ከመውሰድ ይልቅ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ግድየለሽ ሊያስብል ይችላል፡፡*

*ባለፈው ወር ከነሐሴ ፲፪ ቀን ፳፻፲፫ ዓ/ም ጀምሮ በምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት በኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥር ባሉ የገጠር ቀበሌዎች ፀረ ሰላም ኃይሎች በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ በፈጸሙት ጥቃት በርካቶች ለሞትና ለስደት መዳረጋቸውን መዘገባችን ይታወሳል፡፡ከጥቃቱ የተረፉ በርካታ ምእመናንም ተጠልለው በሚገኙባቸው አካባቢዎች ለከፍተኛ ረኀብና የፀጥታ ስጋት እንደተጋለጡ ታውቋል፡፡በኦሮምያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትም ሆነ በፌዴራል መንግሥት ምንም ዓይነት የፀጥታም ሆነ የሰብአዊ እገዛ እየተደረገላቸው እንዳልሆነም ከሥፍራው የደረሱን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡በተለይ ተፈናቃይ ምእመናን አሁንም ድረስ የ”ድረሱልን” ጥሪ እያሰሙ ይገኛሉ፡፡*

*በአካባቢው በፀረ ሰላም ኃይሎች እየተፈጸመ ስላለው አረመኔያዊ ድርጊቶች ዝግጅት ክፍላችን እየተከታተለ ተከታተይ ዘገባዎችን ማቅረቡ ይታወሳል፡፡በዚህ እትማችንም ስማቸው ለጊዜው እንዳይገለጽ ከፈለጉ በምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት አገልጋይ ከሆኑ አባት ጋር በአሁኑ ሰዓት የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ አጭር ቆይታ አድርገናል፡፡ያደረግነውን ቆይታም እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡መልካም ንባብ፡፡*

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** *በዚህ ወቅት በምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥር የሚገኙ ምእመናን በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?*

***የኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት የሃይማኖት አባት፡-*** *በአካባቢው የሚንቀሳቀሰው ፀረ ሰላም ኃይል ከዚህ ቀደም በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን ላይ ጥቃት ማድረሱን ተከትሎ በርካታ ምእመናን ለሞት፣ ለጉዳትና ለስደት ተዳርገዋል፡፡በተለይ ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ ቁጥራቸው ከሦስት እስከ አራት ሺህ የሚሆኑ ምእመናን አካባቢያቸውን ጥለው ተሰደዋል፡፡የተሰደዱት ምእመናንና አገልጋዮች እስካሁን ድረስ ያለ በቂ መጠለያና ምግብ በተለያዩ አካባቢዎች ይገኛሉ፡፡በአሁኑ ወቅት ተፈናቃዮቹ ያሉበት ሁኔታ እጅግ በጣም አሳሳቢ ነው፡፡ሁሉም ተፈናቃዮች ከየአካባቢያቸው በሰላም መደፍረስ ምክንያት ድንገት ሲወጡ ሀብት ንብረታቸውን ትተው በመውጣታቸው ባሉበት መጠለያ ጣቢያ ሕይወታቸውን በባዶ ለመግፋት ተገደዋል፡፡አብዛኛዎቹ በረኀብና በጤና መታወክ ምክንያት ከፍተኛ አደጋ ላይ ወድቀዋል፡፡በአጠቃላይ በኪረሙ ወረዳ የሚገኙ የአምስት ቀበሌ ሕዝበ ክርስቲያን ሀብትና ቤታቸውን ትተው እንደወጡ ቀርተዋል፡፡ከሁለት መቶ በላይ ሲገደሉ ከሦስት መቶ በላይ ምእመናን ደግሞ የደረሱበት አልታወቀም፤ጠፍተዋል፡፡*

*ከነሐሴ ፲፪ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ጀምሮ በፀረ ሰላም ኃይሎች በተፈጸመ ጥቃት ከሞቱና ከተፈናቀሉ ምእመናን በተጨማሪ በቅርቡ ከአሥራ ሰባት ምእመናን በላይ በተለመደ መልኩ በአሰቃቂ ሁኔታ ሕይወታቸው አልፏል፡፡ያለምንም በደላቸው በምእመናን ላይ ይህ ሁሉ በደል ሲደርስ እስካሁን ድረስ ያጽናናቸውና ሰብአዊ ድጋፍ ያደረገላቸው ምንም ዓይነት አካል ያለመኖሩ ያሳዝናል፡፡*

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** *በአካባቢው ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁኔታ ምን ይመስላል?*

***የኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት የሃይማኖት አባት፡-*** *በወረዳው ያሉ አብዛኛው አብያተ ክርስቲያናት ህልውናቸው ተጠብቋል እንዲሁም በክልሉ መንግሥት በኩል የተለየ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል ለማለት ያስቸግራል፡፡በኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት ያሉ አብዛኛዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ በሙሉ ሲዘረፉ ሌሎቹ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ወድመዋል፡፡በውስጣቸው የነበረው ሀብትና ንብረት እንዲሁም ንዋየ ቅድሳት ሳይቀር በሙሉ ተዘርፏል፡፡*

የአንዳንዶቹ አብያተ ክርስቲያናት ጣሪያቸው ሳይቀር ተነቅሎ ተወስዷል።ይህንን ሁሉ የከፋ ድርጊት የፈጸመው ፀረ ሰላም ኃይሉ ብቻ ሳይሆን ከፀረ ሰላም ኃይሉ ጋር በመቀናጀት አፅራረ ቤተ ክርስቲያን ወይም ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀና አመለካከት የሌላቸው የተደራጁ አካላት ጭምር መሆናቸውን መረዳት ችለናል።በአካባቢው ካለው አስፈሪ የፀጥታ ችግር ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ለማጣራትም ሆነ ለተጎጂዎች የዕለት ደራሽ ምግብ ለማቅረብ አልተቻለም።እንዲሁም አብዛኛዎቹ አገልጋይ አባቶች መሰደዳቸውና መገደላቸው ለወደፊቱ በአካባቢው ለሚኖረው ሐዋርያዊ አገልግሎት እንቅፋት ይሆናል።አካባቢው ቶሎ አገግሞ ወደ መደበኛ አገልግሎት እንዲመለስ ለማድረግም ያስቸግራል።

**ስምዐ ጽድቅ፡-** በአካባቢው ያለውን ችግር ሰፋት እንዴት ይገልጹታል?

**የኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት የሃይማኖት አባት፡-** በአካባቢው ያለው ችግር እጅግ ሰፊና ውስብስብ ነው።በአሁኑ ወቅት በአካባቢው የሰውም ሆነ የመኪና እንቅስቃሴ የለም።አካባቢው ሰላማዊ የሆነ የሰው ልጅ ሁሉ በግፍ የሚገደልበት ነው።የችግሩ ስፋትና ውስብስብነት ሀገረ ስብከቱ ከአቅሙ በላይ ስለሆነ ለሚመለከተው አካል ችግሩን ከማሳወቅ ውጭ ሌላ ነገር እያደረገ አይደለም።የኦሮምያ ክልላዊ መንግሥትም የአካባቢውን ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር ያለው ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት አናሳ ከመሆኑም በተጨማሪ ለተጎዱና ለተፈናቀሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሰብአዊ ድጋፍ ለማድረግ ምንም ዓይነት ፍላጎት የለውም።ይህ ደግሞ ተግባሩን መፍትሔ የለሽና ውስብስብ አድርጎታል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰብአዊ ድጋፍ የሚያደርጉ የረድኤት ድርጅቶችና የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ወደ አካባቢው መንቀሳቀሳቸውን ሰምተናል።ይሁን እንጂ አሁን ባለን መረጃ መሠረት ለተጎጂዎችም ሆነ ለተፈናቃዮች ምንም ዓይነት ድጋፍ እንዳልቀረበላቸው ማረጋገጥ ችለናል።የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንም ጉዳዩን እየተከታተለ ለመንግሥት እያሳወቀ ቢሆንም አስፈላጊውን ለውጥ ማምጣትና ተፅዕኖ መፍጠር አልቻለም።የታፈኑ በምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥር በሚገኙ ቀበሌዎች ያሉ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንን ሚዲያዎች ድምፅ ሊሆኑላቸው ይገባል።ቤተ ክርስቲያንም የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳት ለሚመለከታቸው አካላት ማስረዳት አለባት።በዚህ ወቅት እኛ ከሀገረ ስብከት እስከ ማዕከል ድረስ መረጃዎችን የመለዋወጥና የማደራጀት ሥራዎችን እየሠራን እንገኛለን።ይህም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

**ስምዐ ጽድቅ፡-** በአካባቢያቸው ያሉና የተፈናቀሉ ምእመናን ስሜት ምን ይመስላል?

**የኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት የሃይማኖት አባ፡-** በአንዳንድ አካባቢ ያሉ ምእመናንም ሆኑ የተፈናቀሉት ስሜታቸው አንድ ዓይነት ነው።ሁሉም ከምድራዊ ሕይወት ይልቅ ሰማያዊ ሕይወትን ይናፍቃሉ።ሞትን ንቀዋል፤ ለእምነታቸውና ለቤተ ክርስቲያናቸው የታመኑ ሆነዋል።ከምንም በላይ በየዕለቱ የቤተ ክርስቲያናቸውና የእምነታቸው ነገር ያሳስባቸዋል።ከቤተ ክርስቲያናቸው በፊት ለመሠዋት ቆርጠዋል።ቤተ ክርስቲያናቸውን በደማቸው አርነት ሊያወጧት ተፋልመዋል፤ ወደፊትም ይህንን ተጋድሎ ለማድረግ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነዋል።የሚደርስባቸው ምድራዊ ኃይል እንደሌለ በመረዳት አቅማቸው የቻለውን ያህል ተጋድሎ ለማድረግ ተማምለዋል።ራስን ለእምነትና ለቤተ ክርስቲያን ሲሉ አሳልፎ መሥጠት ምን እንደሆነ የዚያ አካባቢ ምእመናንና ካህናት አስተማሪዎች ናቸው።የተፈናቀሉ በርካታ ምእመናንና ካህናት አባቶች ወደቀያቸው ተመልሰው ከሚወዷት ቤተ ክርስቲያናቸው ጋር አብረው ለመቃጠል ወስነዋል።

**ስምዐ ጽድቅ፡-** በአካባቢው ያለው ችግር በፍጥነት መፍትሔ እንዲያገኝ ምን እየተሠራ ነው?

**የኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት የሃይማኖት አባት፡-** በአሁኑ ሰዓት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥት ባለ ሥልጣናት ጋር እየተወያዩ ይገኛሉ።ይሁን እንጂ ተፈላጊውን ያህል አስቸኳይ መፍትሔ አልተገኘም።ብፁዕነታቸው በአካባቢው በፀረ ሰላም ኃይሎች አማካይነት የተፈጸመውን ጥፋት በዝርዝር ለመንግሥት ባለሥልጣናቱ አስረድተዋል።የሞቱትን ምእመናን፣ የተፈናቀሉትንና የወደሙ አብያተ ክርስቲያናትን በተመለከተና የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን የወደፊት ዕጣ ፋንታ ምን ሊሆን እንደሚገባ መክረዋል።በተለይ ለተጎጂዎች አስቸኳይ ርዳታ እንዲደረግላቸውና በአካባቢው ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት እንዲመጣ ጠይቀዋል።

**ስምዐ ጽድቅ፡-** በአካባቢው ዘላቂ መፍትሔ እንዲመጣና ምእመናንም ያለ ፀጥታ ሥጋ በነጻነት እንዲኖሩ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

**የኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት የሃይማኖት አባት፡-** እንደሚታወቀው በተፈጠረው ችግር ምክንያት በርካታ ምእመናን በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል፤ ሌሎቹም ሀብት ንብረታቸውን ትተው አገራቸው ወደመራቸው ቦታ ተሰደዋል።የተሰደዱትም በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንደሚኙ ይታወቃል።የአካባቢው ሰላም ተመልሶ እነዚህ አካላት ወደ አካባቢያቸው ቢመጡም የሚቋቋሙበትና የዕለት ጉርስ የማያገኙ በመሆናቸው የወደፊት ሕይወታቸውም አሳሳቢ ነው።አርሰው እንዳይበሉ ፀረ ሰላም ኃይሉ ከብቶቻቸውን ወስዶባቸዋል፤ የዕለት ጉርስ እንዳይኖራቸውም ጎተራቸውን ገልብጠው ጭኖባቸዋል።

ስለሆነም መንግሥት የምእመናኑን ተደራራቢ ችግር በመረዳት አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል።ከሁሉም በላይ ግን የአካባቢውን ሰላም መመለስ የመጀመሪያ ተግባር ሊያደርግ ይገባል።እስካሁን ድረስ ወደ

*ቀያቸው የተመለሱ ምእመናን ባይኖሩም በቅርቡ ሁሉንም ምእመናን ወደ መኖሪያ አካባቢያቸው ለመመለስ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አውቀናል::መንግሥት የሴቶችን፣ የሕፃናትንና የአረጋውያንን ሰቆቃና ሕመም ተረድቶ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በቶሎ ወደ ቀያቸው እንዲመልሳቸው መልእክቴን አስተላልፋለሁ::*

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** *በፀረ ሰላም ኃይሎች በተፈጸመ ጥቃት የተሠዉ አገልጋዮች ምን ያህል ናቸው? ለእምነታቸውና ለቤተ ክርስቲያናቸው ያደረጉት ተጋድሎስ ምን ይመስል ነበር? ሌላውስ ከእነርሱ ተጋድሎ ምን ይማራል?*

***የኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት የሃይማኖት አባት፡-*** *እንደሚታወቀው ቤተ ክርስቲያናችን የተመሠረተችውና እስከ ዛሬ ድረስ ፀንታ የቆመችው በፈተና ውስጥ በማለፍና ቅዱሳን ሰማዕታት በከፈሉት ሰማዕትነት ነው::ቅዱሳን ሰማዕታቱ በከፈሉት የደም ዋጋ ቤተ ክርስቲያናችን ከክብሯ ሳትወርድ እስከ ዛሬ ድረስ ሐዋርያዊ ተልኮዋን እየፈጸመች ትገኛለች::ለዓለም ብርሃንም ሆናለች::ከአበውና ከቅዱሳን ሰማዕታት በወረሱት ተጋድሎ በዚህ ዘመን ያሉ ምእመናንና ካህናት አባቶች እምነታቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን ለማርከስ የመጣን ፀረ ሰላም ኃይል ፊት ለፊት በመጋፈጥና መሥዋዕት በመሆን ወደ ጽድቅ መንገድ ሲጓዙ ተመልክተናል::ሰሞኑንም በምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥር በሚገኙ ቀበሌዎች የሚኖሩ ምእመናን ቤተ ክርስቲያናቸውንና እምነታቸውን ሊያረክስ ከመጣ ፀረ ሰላም ቡድን ጋር በባዶ እጃቸው ፊት ለፊት ተጋፍጠው ወደማይቀረው ዓለም በክብርና በሞገስ ተሸኝተዋል::በተለይ በኪረሙ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥር ያገለግሉ የነበሩ አባቶች ካህናትና መነኰሳት ብቻቸውን ቤተ ክርስቲያናቸውን ከፀረ ሰላም ኃይሉ ጥፋት ለመጠበቅ ተጋድሎ እያደረጉ እያለ በክብር ተሠውተዋል::የክብርን ሞት ሞተዋል፤ ሰማያዊ አክሊልንም ተጎናጽፈዋል::*

*በአካባቢው የሚኖሩ አንዳንድ ምእመናን የፀረ ሰላም ኃይሉን እኩይ ድርጊት በመስጋት የተሻለ ደኅንነት ወደአለበት አካባቢዎች በሸሹበት ወቅት ካህናትና መነኮሳቱ ግን ‹‹ከቤተ ክርስቲያኔ በፊት እኔን›› ብለው የማይተካውን ውድ ሕይወታቸው ገብረዋል::ተግባራቸውም ለትውልድ ይነገራል::መጪው ትውልድም ከእነዚህ አባቶች በረከት ያገኛል፤ ያደረጉት ታላቅ ተጋድሎም ለትውልዱ ትምህርትም ጽናትም ነው ትምህርት::ለሃይማኖታቸውና ለቤተ ክርስቲያናቸው ሲሉ ለተሠዉ ካህናት፣ አባቶችና ምእመናን መስታወሻ እንዲቆምላቸው እና በጸሎት እዲታዲታወሱ መደረግ አለበት::ረጎብ ጊዜ አይሰጥምና ከሞቀ አካባቢያቸው ወጥተው ለተፈናቀሉ ምእመናን ሰብአዊ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል::ጠቅላይ ቤተ ክህነት አቅም፣ሥልጣንና ተደማጭነት ያለው አካል በመሆኑ ከሀገሪቱ መንግሥት ጋር በግልጽ በመነጋገር ዘላቂ መፍትሔ እንዲመጣ መሥራት ይኖርበታል::በአጠቃላይ በሕይወት ለተረፉ ምእመናን አስፈላጊውን ሁሉ ጥበቃ እንዲደረግላቸውም እናሳስባለን::*

*በአባቶቻችን ብሂል ‹‹መሀሉ ዳር ይሆናል›› እንደሚባለው መሀል ሀገር ላይ በተደላደለ የፀጥታ ሁኔታ ያሉ ምእመናንና አገልጋይ አባቶች ከኪረሙ ወረዳ ካህናት አባቶችና ምእመናን ተጋድሎ ትምህርት ወስደው ራሳቸውን ለፈተናና ለፅናት ማዘጋጀት አለባቸው::በኪረሙ ወረዳ የደረሰው ሰቆቃ ወደመሀል ሀገር የማይሄድበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለምና ለተጋድሎ ራስን ማዘጋጀት ተገቢ ነው::የመጣውን ፈተና ሁሉ ፊት ለፊት ሳንጋፈጥ ቤተ ክርስቲያንን ለትውልድ ማስተላለፍ አንችልም::ከአባቶቻችን ከነክብሯ የተቀበልናትን ቤተ ክርስቲያን በተጋድሎ ለመጭው ትውልድ ማስተላለፍ ካልቻልን የታሪክ ተወቃሽ እንሆናለን::የሰማዕታት አባቶቻችን ደምና አጥንትም ይወቅሰናል::*

> **በአካባቢው የሚኖሩ አንዳንድ ምእመናን የፀረ ሰላም ኃይሉን እኩይ ድርጊት በመስጋት የተሻለ ደኅንነት ወደአለበት አካባቢዎች በሸሹበት ወቅት ካህናትና መነኮሳቱ ግን ‹‹ከቤተ ክርስቲያኔ በፊት እኔን›› ብለው የማይተካውን ውድ ሕይወታቸው ገብረዋል::**

# የመስከረም ፳፩ ክብረ በዓል በግሸን ተራራ

ምኒልክ ብርሃኑ

*ልጆችዬ እንደምን ቆያችሁ! እግዚአብሔር ይመስገን በጣም ደኅና ነን::የመስቀል በዓልን እንዴት አከበራችሁ? በቅዳሴ፣ በመዝሙር፣ ዳመራ በማብራት እንዳከበራችሁ እርግጠኞች ነን::*

ልጆች! አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል (የመስቀል ክፋይ) የት እንደሚገኝ ታውቃላችሁ?.......አዎ ልጆችዬ! ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል በአገራችን ኢትዮጵያ ይገኛል::የሚገኝበት ቦታ ደግሞ ግሸን በሚባል ተራራ ላይ ነው::በዚህ ተራራ ላይ ደግሞ የእናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን አለ::ዛሬ መስቀሉ እንዴት ወደ አገራችን እንደመጣ፣ በግሸን ተራራ ላይ መስከረም ፳፩ ቀን ስለሚከበረው በዓል እንማራለን::በጥሞና ተከታተሉን እሺ!

## ቅዱስ መስቀሉን እንደተከፋፈሉት

ልጆችዬ! ባለፈው እንደተመለከትነው ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ክፋዮች እንደቀበሩት፤ በንግሥት ዕሌኒ አማካይነት ከተቀበረበት እንደወጣና ኢየሩሳሌም ውስጥ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶለት እንደተቀመጠ አይተናል::ታዲያ ልጆች ከዚህ በኋላ ቅዱስ መስቀሉ ብዙ ተአምራትን በማድረግ ሰዎችን ከሞት ያስነሣል፣ ከበሽታ ያድናቸዋል::ይኽንን ተአምራት የሰሙ ደግሞ በመስቀሉ ለመባረክ ከተለያየ አገር ወደ ኢየሩሳሌም ይመጡ ነበር::

በኋላ ግን አንድ አስደንጋጭ ነገር ተፈጠረ::እሱም ከሌላ አገር የመጡ ሰዎች መስቀሉን ሊወስዱት ፈለጉ::በዚህም የተነሣ ብዙ ክርክር ተደረገ::ከዛም የሃይማኖት አባቶች መጡና መስቀሉን ለአራት ለመካፈል ተስማሙ::በዚህ መሠረት በቀኝ ክንፍ የሚገኘውን የመስቀሉ ክፋይ በግብፅ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ወሰዱት::የግራውንም፣ ከላይና ከታች ያለውን ክፍል ደግሞ የኢየሩሳሌም፣ የቱርክና የሮም ክርስቲያኖች ወሰዱት::ከዚያም በግብፅ የሚኖሩ ክርስቲያኖች መስቀሉን ወደ አገራቸው ወሰዱትና በክብር አስቀመጡት::

ልጆች! ይኽንን ታሪክ አስተዋላችሁ፤ ብዙ ሰዎች በመስቀሉ ለመባረክ ስለሚፈልጉ ወደ አገራቸው እንዲመጣ ይፈልጉ ነበር::ይኽንን የተረዱ ታላላቅ አባቶች በዓለም ያለ ሕዝብ እንዲባረክና ለብዙዎችም እንዲዳረስ አስበው መስቀሉን አካፈሉና ሰጡ::አያችሁ አይደል! እኛም ልክ እንደነርሱ መባረክ ስላለብን መስቀሉን የያዙ አባቶችን ስናገኝ መሳለም አለብን::ይኽን ስናደርግ እንባረካለን፤ እግዚአብሔርም ከብዙ ነገር ይጠብቀናል::

## በግብፅ ክርስቲያኖች ላይ መከራ እንደደረሰ

ልጆች! መስቀሉ ወደ ግብፅ እንደመጣ ክርስቲያኖችን እየባረከ ይጠብቃቸው ነበር::ከብዙ ጊዜ በኋላ ግን መጥፎ ንጉሥ በግብፅ ላይ ነገሠ::ታዲያ ይኽ ንጉሥ ክርስቲያኖችን ያሳድዳቸው፣ ይገድላቸው፣ ከባድ መከራም ያደርስባቸው ጀመር::እነርሱም ከዚህ መከራ የሚያድናቸው ሰው ይፈልጉ ነበር::

በዚህ ጊዜ ደግሞ በኢትዮጵያ ዐፄ ዳዊት የሚባል ታላቅና ጥሩ ንጉሥ ነግሦ ነበር::ይኽ ንጉሥ እጅግ በጣም የሚያስፈራ፣ ስሙ በዓለም ሁሉ የገነነ እግዚአብሔርን የሚፈራ ጠንካራ ንጉሥ ነበር:: በግብፅ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ደግሞ የዐፄ ዳዊትን ዝና ስለሰሙ ከመጥፎ ንጉሥ እንዲያድናቸውና እንዲጠብቃቸው በደብዳቤ መልእክት ላኩ::

## ዐፄ ዳዊት ክርስቲያቾን ለማዳን እንደተነሣ

በዚህ መሠረት ዐፄ ዳዊት የግብፅ ክርስቲያኖችን ነጻ ለማውጣት ተነሣ::በርካታ ሠራዊቱንም አሰልፎ፣ በፈረስና በቅሎ ታጅቦ፣ ጦርና ጋሻ ይዞ በሚያስፈራ ግርማ ሞገስ ወደ ግብፅ መሔድ ጀመረ::ልጆችዬ የሚገርመው ገና ዐፄ ዳዊት በመንገድ እያለ የግብፅ ንጉሥም ወደርሱ እንደሚመጣ ባወቀ ጊዜ እጅግ ፈራ::መጥቶም እንደሚያሸንፈው ስላወቀ ልቡ ደነገጠ::ከዛም ክርስቲያኖችን ጠርቶ "ቶሎ ንጉሡን እንዲመለስ ካደረጋችሁ እናንተ ላይ የማደርሰውን መከራ አቆማለው::በነጻነትም መኖር ትችላላችሁ" ብሎም ቃል ገባላቸው::

በዚህ ጊዜ የሃይማኖት አባቶች ለንጉሥ ዳዊት መከራው እንደቀረላቸውና ግብፅን ከመውጋት እንዲቆጠብ መልእክት ላኩ::ዐፄ ዳዊትም ከነሠራዊቱ ጉዞውን አቋርጦ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ::ክርስቲያኖችም በሰላም መኖር ጀመሩ::

## ቅዱስ መስቀሉ ወደኢትዮጵያ እንደመጣ

ከቆይታም በኋላ የግብፅ ክርስቲያኖች ለኢትዮጵያ ንጉሥ ዐፄ ዳዊት ነጻ ስላወጣቸው የሚያማምሩ ጌጣጌጦችንና ወርቆችን በስጦታ መልክ አመጡለት::ንጉሡ ዳዊት ግን "እኔ ብርና ወርቅ አልፈልግም፤ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል ነው የምፈልገው" አላቸው::እነርሱም ያደረገላቸውን ውለታ አስበው ቅዱስ መስቀሉን ሰጡት::ዐፄ ዳዊትም መስቀሉን ወደ አገራቸው ኢትዮጵያ ይዞት መጣ::

ልጆች! ዐፄ ዳዊት ከብርና ከጌጣጌጥ ይልቅ ትልቅ ዋጋ ያለውን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ መስቀል አስበልጦ ለእኛ አመጣልን::ከዚህ ታሪክ የምንማረው ቁም ነገር ሁል ጊዜ ማሰብ ያለብን ታላላቅ ዋጋ ያላቸውን ነገሮችን ነው::ምድራዊ ለሆኑ ለሚጠፉ፣ ለሚያልቁ ነገሮች ሳይሆን ትልቅ ዋጋ ያላቸውን፣ ትልቅ ቦታ የሚያደርሱንን ነው::ሁሌም ቢሆን ትናንሽ ነገሮችን የምናስብ ከሆነ የምናገኘው ትንሽ ነው::ትልቅ ካሰብን ግን ትልቅ ቦታ እንደርሳለን::ስለዚህ ዐፄ ዳዊት ትልቅ ስላሰበ ትልቁን የአምላካችን መስቀል ለእኛ አመጣል::

## መስቀሉ በግሸን ተራራ ላይ እንደተቀመጠ

መስቀሉ ወደ አገራችን ከመጣ በኋላ በግሸን ተራራ ላይ ተቀመጠ::ልጆች ግሸን ተራራ የሚገኘው በወሎ ክፍለ አገር፣ አምባሰል በሚባል ወረዳ ውስጥ ነው::የተራራው ቅርጽ ደግሞ የመስቀል ቅርጽ ይመስላል::ስለዚህ መስቀሉ የመስቀል ቅርጽ በሚመስለው ግሸን ተራራ ላይ ተቀምጦ ይገኛል::ልጆች ይገርማል አይደል! በመስቀለኛ ቦታ ላይ መስቀሉ ሲቀመጥ በጣም የሚያስደስት ነገር ነው::መስቀሉ በግሸን ተራራ ላይ መስከረም ፳፩ ቀን ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶለት በክብር ተቀመጠ::

በዚህ ተራራ ደግሞ የእናታችን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል::ታዲያ ልጆች በዚህ ተራራ ላይ መስከረም ፳፩ ቀን የእመቤታችንን ዓመታዊ በዓልና ቅዱስ መስቀሉ ያረፈበትን ቀን ታሳቢ በማድረግ በታላቅ ድምቀት ይከበራል::ብዙ ሰዎችም በዓሉን ለማክበርና በመስቀሉ ለመባረክ በየዓመቱ መስከረም ፳፩ ቀን ወደ ግሸን ተራራ ይወጣሉ::በዓሉንም በቅዳሴ፣ በዝማሬ፣ በታላቅ ደስታ ያከብሩታል::እናንተም ስታድጉ ወደ ግሸን ተራራ ላይ በመሔድ በመስቀሉ እየተባረካችሁ የእመቤታችንን ቅድስት ድንግል ማርያምን በዓል ማክበር እንዳትረሱ::

በሉ ልጆች! ለዛሬ በዚህ ይብቃን::ስለነበረን ቆይታ አምላካችን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን::በሚቀጥለው ጊዜ በሌላ ታሪክ እስከምንገናኝ ደና ሁኑ::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# የቤተ ክርስቲያን በሮች ስምና ግብር ወዴት... ወዴት?

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

አባቶቻችን የሠሩልን ሥርዓት ምን ያህል ክቡርና ውድ እንደሆነ ሁሉ እንዲያስተውል ብርቱ ምኞት አለኝ::ያለምክንያት የተሠራ ሥርዓት አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን ትርጉምና ጥቅም ያላቸው መሆናቸው የበለጠ ያስደምማል::

ሕንጻ ቤተክርስቲያን ሲሠራ የታወቀ የበሮች ቁጥር፣ የበሮች ስያሜና አጠቃቀም ሥርዓት አለ::ክብ ቤተ ክርስቲያንሲሆንአራትበሮችይኖሩታል::በደቡብለሴቶች መግቢያ፣ በሰሜን ለወንዶች መግቢያ፣ በምሥራቅ ለካህናት መግቢያ ይሠራል::በተጨማሪም በምዕራብ በኩል ሰፋ ተደርጎ የተሠራ ሆኖ በበዓላትና በሰንበት የጋራ መውጫ በር ሆኖ ሊያለግል የሚችል በር አለ::

በቤተ ክርስቲያናችን የሴቶችና የወንዶች የምስጋና ሥርዓት መነሻ ተደርጎ ይህ ስያሜና አጠቃቀም ይኑር እንጂ በጥንትም በእስራኤል ሥርዓት የኢየሩሳሌም በሮች ስያሜና ልዩ ልዩ ጥቅም ነበራቸው::መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይላል፤ ‹‹የከተማይቱ በሮች እንደ እስራኤል ነገዶች ስም ይሆናሉ በሰሜን በኩል አንዱ የሮቤል በር አንዱም የይሁዳ በር አንዱም የሌዊ በር፥ ሦስት በሮች ይሆናሉ::በምሥራቁም ወገን አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ፥ ሦስትም በሮች አሉ፤ አንዱ የዮሴፍ በር አንዱም የብንያም በር አንዱም የዳን በር ነው::በደቡብም ወገን ልኩ አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ፥ ሦስትም በሮች አሉ፤ አንዱ የስምዖን በር አንዱም የይሳኮር በር አንዱም የዛብሎን በር ነው::በምዕራቡም ወገን ልኩ አራት ሺህ አምስት መቶ ክንድ፥ ሦስትም በሮች አሉ፤ አንዱ የጋድ በር አንዱም የአሴር በር አንዱም የንፍታሌም በር ነው:: /ሕዝ ፵፰፥ ፴፩-፴፬/ በማለት እስራኤል በአራት አቅጣጫ የሚገቡበት በር ነበር::ያንን መነሻ ያደረገና ከዚያም በተሻለ ምሳሌና ትርጓሜ የሕንጻ ቤተክርስቲን በሮች በአራት አቅጣጫ ይሠራሉ::

ከዋሻ ቤተክርስቲያን በስተቀር በሌሎች ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት ይህ ሥርዓት ተከብሮ ይሠራል::የዋሻ ቤተክርስቲያን ሲሆን የሚኖረውም በር አንድ ነው::አብዛኞቹ የዋሻ አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉት በገዳማት ነው::በገዳማት ያሉ ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናትን ዕለት ዕለት የሚጠቀሙባቸው ደግሞ ገዳማውያኑ ናቸው::ገዳማውያን ደግሞ አንዳንድ ገዳም ላይ የወንዶችና ሴቶች ተብለው ስለሚለዩ በጾታ የተከፈለው የሕንጻ አብያተክርስያናቱ በሮች አገልግሎት ሥርዓቱ ከተሠራበት ዓላማ አንጻር ዋሻ ቤተ ክርስቲያን አንድ በር መሆን ችግር አይፈጥርም::ይህም ሁሉም ጾታ ምእመናን መንግሥተ ሰማያትን አንድ ሆነው የመውረሳቸው ምሳሌ ሲሆን ጥንታዊውን የግበበ ምድር የክርስቲያኖች ኑሮና ተጋድሎም ለማሰብ ነው::

አብዛኞቹ የገጠር አብያክርስቲያናትና አድባራት ግን በክብ ቅርጽ ወይም በሰቀልማ የሚሠሩ በመሆኑ ሥርዓቱ በሚያዘው መንገድ አራት በሮች ኖሯቸው ይሠራሉ::በእነዚህ በሮችም ምእመናን በየጾታቸው ቆመው በቅድስትና በቅኔ ማኅሌት እንዲሁም ካህናቱ በመቅደስ አገልግሎት ይሰጡበታል፤ ይቀበሉበታል::በምዕራብ አቅጣጫ ባለው ቅድስት ቆሞሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ ልዑካን ቀዳስያን፣ መምህራነ ወንጌል ሙሽሮች አገልግሎት ለመስጠት ለመቀበል ይቆሙበታል::በደቡብ በኩል ባለው ቅድስት በደቡብ የሴቶች በር የገቡ ደናግል መነኮሳዪያት፣ የቀሳውስትና የዲያቆናት ሚስቶች፣ የሚቆርቡ ሴቶች አገልግሎት ለመቀበል ይቆሙበታል::በሰሜን ባለው ቅድስት ደናግል መነኮሳት የሚቆርቡ ወንዶች ምእመናን ለማስቀደስ፣ ለመጸለይ ለመቁረብ ወዘተ በዚያ ይቆሙበታል::እነዚህ በጾታ የተከፋፈሉ

ምእመናን በራሳቸው ረድፍ ተመስጠው ለጸሎት እንዲቆሙ በመጋረጃ ይለያሉ።በቅኔ ማሕሌትም እንዲሁ የራሱ ሥርዓት ባለው መንገድ አገልግሎት ይሰጥበታል።(የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት)

ይሁን እንጂ ከጊዜ ጊዜ ይህ ሥርዓት በተለያዩ ምክንያቶች እየተሸረሸረ መምጣቱን በትዝብት ለማየት ቀላል ሆኗል።በአንድ በኩል በርካታ ምእመናን የሕንጻ ቤተክርስቲንን በሮች ሥርዓታዊ ፋይዳቸውን፣ ምሳሌያዊና ምሥጢራዊ ይዘታቸውን ባለማወቅ እንደ ልባቸው መሻት ሲጠቀሙበት ይታያሉ።በሌላ በኩል ደግሞ አውቀው በድፍረትና በግዴለሽነት አገልጋዮች ያስከተሉት ችግርም አለ።

በዚህም ምክንያት ወንዶች በሴቶች በር፣ ሴቶች በወንዶች በር ሲገቡ ይስተዋላል።ከካህናትም ወገን የራሳቸው ከሥልጣናቸው ጋር የተባበረ በምሥጢር የከበረ መግቢያ እያላቸው በምእመናን መግቢያ ሲገቡ ይስተዋላል። በዚህ ሳይበቃ ከገቡ በኋላ ሴቶች በሚቆሙበት ወንዶች፣ ወንዶች በሚቆሙበት ሴቶች እየተደባለቁ ሲቆሙ ማየት እየተለመደ ነው።በተለይ ዘመናዊ ሆነው ተሠሩ በሚባሉ፣ ሰቀልማ ዓይነት ቅርጽ ባላቸው ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት በመጋረጃም ተለይተው ባለመደራጀታቸው የሴቶች መግቢያ የሆነው የደቡብ በር የሁሉም የጋራ መግቢያ እንዲሆን የታዘዘ እስኪመስል የሥርዓት አለመጠበቅ ይታይበታል። በአንድ በር የገቡ ሁለቱም ጾታዎች ተቀላቅለው መቆማቸው ምንም እንዳይሰማቸው እያደረገ ነው።

በክብ አብያተ ክርስቲያናት በተወሰነ መልኩ በመጋረጃ በተለየው የሴቶችና የወንዶች መቆሚያ ይህ ችግር በስፋት እንዳይታይ ሆኗል።በሌላው የሰቀልማ አብያክርስቲናት ውስጥ ግን ሰፋፊ ሕንጻ አብያተ ክርስቲያናት ሴቶችና ወንዶች ተደባልቀው መቆማቸውን በግልጽ የምናይበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው።

ይህ ብቻ ሳይሆን በአግባቡ አልባሳትን ባለመልበስ ሰውነትን የሚያራቁት፣ ፀጉርን በአግባቡ በማይሸፍን፣ በጌጣጌጥ የተንቆጠቆጡ ሴቶች ለጸሎት የታደሙ ምእመናንን ሁሉ ሲገቡና ሲወጡ፣ በዚያ ተደባልቀው ሲቆሙ ምእመናንን ማወካቸው አልቀረም።በዚህም ምክንያት የጸሎት ቤት በሆነችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ሐሳብን ሰብስቦ ከፍትወተ ሥጋ ርቆ ለአፍታም ቢሆን ለመቆም አለመቻልን ያስከትላል።ሴቶችና ወንዶች እየተያዩ ቆመው የሚያወሩበት፣ መልእክት የሚለዋወጡበት፣ አንዳንድ ሴቶች ደግሞ ከለበሱት ልብስ ብቻ ሳይሆን ከተቀቡት ሽቶ የተነሣ ሌሎችን የሚያውኩበት ዕድል ሰፊ እየሆነ ነው።

ይህ የሥርዓት አለመጠበቅ ችግር በዓለ ንግሥ በሚሆንበትና በሥርዓተ ተክሊል ጊዜ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የባሰ ችግር ይፈጥራል።ምእመናን በዚህ ዓለም ሲኖሩ ከልዩ ልዩ ሥጋዊ ሐሳብ ርቀው ቅድመ እግዚአብሔር የሚቆሙበትን ያቺን የተወደደች ሰዓት በሥርዓት እንዲንከባከቧት አባቶቻችን የሠሩት ሥርዓት እየተጎዳ ነው።ለብዙ ትዝብትም እየዳረገ ነው።

ስለዚህም በቅድሚያ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ይሆናል።አውቀው የሚያጠፉትን ደግሞ መገሠጽ ይገባል።ሥርዓቱ ከሚከበርባቸው በማስተዋል ከሚመሩ አትቢዎችም ትምህርት ሊወስዱ ይገባል።ሥርዓቱ እግዚአብሔርን ማክብር የምናሳብትም ስለሆነ ትሕትናን መላበስ ያስፈልጋል።በልማድ ለሚመላለሱ መንፈሳዊ ሕይወትን በጥንቃቄ ለመያዝ ላልታደሉ ሰዎች ይህ ነገር ዘበት ሊሆን ይችላል።የጸሎት፣ የቅዳሴ፣ የዝማሬ ጊዜቸያው ግን ውድና የተከበረ፣ የበረከትና የሕይወት ነገር መሆኑን አምነው ለሚኖሩ ግን ቁጭት የሚፈጥርና መረበሽን የሚያስከትል ነው።ስለዚህም በትምህርትና ተግሣጽ ፈጥኖ ማስተካከል የሚበጅ ነው እንላለን።

# ማዕተብ ሳይኖር ክርስቲያን መሆን አይቻልምን?

**ክፍል ሁለት**

***የተወደደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ቀጣዩንና ሁለተኛውን ክፍል ደግሞ እነሆ ፦***

"ሥራሽ ያውጣሽ" ተብላ ከባሕር የተጣለችዋ ዕሌኒ ከባሕሩም ወጥታ እግዚአብሔርን ከማያመልክ ሰው ጋር በትዳር አንድ ሆና፣ ቆስጠንጢኖስን ወለደች፡፡ምንም ከማያምን ሰው ብትወልደውም ከማያምን ጋር ሆኜ ምን አደርጋለሁ ሳትል ልጇን በጥበብና በፈሪሃ እግዚአብሔር አሳደገችው፡፡ልጅዋም በመከራ ውስጥ የነበረችዋን ቤተ ክርስቲያን ነጻ አወጣት፤ እርሷም ለሦስት መቶ ዓመት ያህል ተቀብሮ የኖረውን መስቀል ከተቀበረበት አወጣችው፡፡ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት እያለች ታከብራታለች፡፡የንጉሡን የቆስጠንጢኖስንም ታሪክ በክብር ጽፋ ስታዘክረው ትኖራለች፡፡ስለዚህ እንደ ንግሥት ዕሌኒ በሌላ እምነት ካለ ሰው ጋር ለጊዜው በትዳር ሕይወትሽ አንድ ብትሆኚ ነገሮችን ሁሉ ለመልካም አጋጣሚ መጠቀም ከቻልሽ የእግዚአብሔር የድንቅ ሥራው መገለጫ ትሆኚለሽና መበርታት ያስፈጋል፡፡

መ. በትዕግሥት እርሱን አሳምኖ ለመመለስ ከፍተኛ ጥረት ቢደረግ፡- ሰው የሚገጥመውን ሁሉ ችግር በትዕግሥት ሲያልፍ የማይታየውንና ዘለዓለማዊውን በሚታየው ግን ጊዜያዊ በሆነው ለውጦ ነው፡፡ስለዚህ ችግሮቹ ሊደራረቡ ይችላሉ፡፡ይሁን እንጂ የማያልፍና ዘለዓለማዊ የሆነ ለጊዜው ግን የማይታይ ሀብት አለንና በትዕግሥት መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ይህን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ምእመናን በላከው መልእክቱ "የሚታየውን ተስፋ ማድረግ ተስፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ እንዴት ተስፋ ያደርጋል? እንዴትስ ይጠብቃል? የማይታየውን ተስፋ ብናደርግ ግን እርሱን ተስፋ አድርገን በእርሱ እንደ ጸናን መጠን ትዕግሥታችን ይታወቃል" (ሮሜ ፰፣፳፬-፳፭) በማለት አስረድቶናል፡፡

የልጆችንም ሆነ የአንቺን እንዲሁም የእርሱን ሕይወት ለማቃናት እንደ አንድ መደበኛ ተግባር መመልከትና ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ብዙኃኑ የሚያስቀድመው የጊዜያዊውንና የሥጋዊውን ጉዳይ ነው፡፡ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ምንመገበው፣ ስለምንጠጣው፣ ስለምንለብሰው ሁሉ መጨነቅ እንደሌለብን በሚገባ አስተምሯል፡፡"እናንተስ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል" (ማቴ. ፮፣፴፫) እንዲል፡፡ይህ ማለት የምንበላውንና የምንጠጣውን ማሰብ የለብንም ማለት አይደለም፡፡ከመንግሥተ ሰማያት ማለትም ከነፍሳችን ጉዳይ ግን ሊበልጥብን አይገባም፡፡

ስለሆነም እኅታችን አሁን በሆነ ነገር ላይ ነው እየተወያየን ያለነውና ትዳርሽን ወደ መፍታትም ሳትቸኩይ፣ ደግሞ ከቤቴና ከልጆቼ ጋር በተገናኘ ለጊዜው ተመችቶኛልና ለጊዜው ከተመቸኝ ምን አገባኝም ሳትይ የዘወትር ጸሎትሽ፣ የዕለት ተለት እንቅስቃሴሽ ባለቤትሽን ለማሳመን፣ ልጆችሽንም በፈሪሃ እግዚአብሔር፣ በጥበብና በሞገስ ለማሳደግ፣ ጥረት ማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡

ከአሕዛብ ጋር እየኖሩ ሕይወታቸውን በአግባቡ የመሩ፣ ከትልቁ የቅድስና ሕይወት የደረሱ በርካታ ሰዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ሙሴ ከፈርኦን ቤት በቤተ መንግሥት ነው ያደገው፤ አሳዳጊዎቹ እናትና አባቱ ግን ሀልዎተ እግዚአብሔርን፣ ነገረ ቅዱሳንን ፣ ትምህርተ ሃይማኖትን ወዘተ . . . እያስተማሩ በፈሪሃ እግዚአብሔር አሳደጉት፡፡ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ እንደነገረን በእምነት ካደገ በኋላ የፈርኦን የልጅ ልጅ መባልን አልወደደም፤ በፈርኦን ቤት በምቾት ከመኖር ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ (ዕብ.፲፩፣፳፫-፳፰)፡፡በአሕዛብ ቤት ቢያድግም ትዕግስትን ገንዘብ በማድረጉ እስራኤል ከግዞት ለመውጣታቸው ምክንያት ሆነ፡፡ስለዚህ የቅዱሳን አባቶችንና እናቶችን የሕይወት ልምድ አብነት በማድረግ ከጊዜያዊ ጭንቀት በመውጣት ዘላቂ ተግባር ለመሥራት መትጋት፣ ተግባሮቻችን በአጭር ጊዜ፣ በመካከለኛ ጊዜና በረጅም ጊዜ ሊከናወኑ የሚችሉትን በመለየት መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡

ሠ. የማዕተብን ምንነት፣ አስፈላጊነትና ቢቀር የሚያስከትለውን ውጤት መረዳት

**፩. የማዕተብ ምንነት**

ማዕተብ ማለት ምልክት ወይም ማማተብ ማለት ነው (ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ሀብተ ሚካኤል የአማርኛ መዝገበ ቃላት ገጽ ፯፶)፡፡የምን ምልክት ነው ከተባለ ደግሞ ሰዎች በአርባ በሰማንያ ቀናቸው በስመ ሥላሴ ተጠምቀው ከሥላሴን ልጅነትን ሲቀበሉ በክርስቶስ ክርስቲያን፣ በወልድ ውሉደ እግዚአብሔር፣ በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳውያን ለመባላቸው በአንገታቸው የሚታሰር ምልክት ነው፡፡ይህን በተመለከተ ወይዘሮ ዘውዴ ገ/ እግዚአብሔር ማዕተብና ክርስትና በተሰኘ መጽሐፋቸው "ማዕተብ ተጠምቀን የሥላሴን ልጅነት ስናገኝ እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምታጠልቅልን እስከ ዕለተ ሞታችን ድረስ የምንጠብቀው የማይበጠስ የማንነታችን መለያ ምልክት ነው፡፡የአንድ ሀገር

ባንዲራ የዚያችን ሀገር ክብሯን፣ ሉዓላዊነቷንና በአጠቃላይ ሀገሪቷን እንደሚወክል ሁሉ ማዕተብም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እምነታቸውንና ማንነታቸውን የሚገልጽ ወካይ አርማቸው ነው” (፳፻፰ዓ.ም. ገጽ ፲፰) በማለት ገልጸዋል፡፡

ስለዚህ ማዕተብ የክርስትናችን መለያ፣ የማንነታችን መመስከሪያ፣ ምልክታችን፣ አርማችን ነው፡፡ይህ ማዕተብ በራሱ ብቻውን ክርስቲያን ያደርገናል ማለት አይደለም፡፡ከላይም እንደተገለጸው በስመ ሥላሴ የተጠመቀ ሰው ለመጠመቁ፣ በክርስቶስ ስም ተጠርቶ ክርስቲያን ለመሰኘቱ ምልክት ነው፡፡መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተቀበለውን መከራ ልናዘክርበት፣ በስሙ ማመናችንን ልንመሰክርበትና የክርስቶስ ተከታዮች ለመሆናችን ምልክት ይሆነን ዘንድ በአንገታችን እናጠልቀዋለን፡፡

**፪. የማዕተብ አስፈላጊነት**

ማዕተብ ከላይ ምንነቱን እንደተመለከትን ሁሉ አስፈላጊነቱንም ስንመለከት ከምንነቱ በመነሣት የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

**ሀ. ከአሕዛብና ከመናፍቃን ተለይተን እንታወቅበታለን፦** ነቢዩ ኢዩኤል እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲያስተላልፈው የገለጸለትን ቃል “ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ” (ኢዩ.፪፣፲፫) በማለት እንደነገረን ከምንም በላይ ውስጣዊ ማንነታችንን ለእግዚአብሔር ምቹ ማድረግ የግድ ቢሆንም ለውስጣዊ ማንነታችን መገለጫ የሆነው ውጫዊ ማንነታችንም በአግባቡና በሥርዐቱ ሊመራ ይገባዋል፡፡ስለዚህ ኦርቶዶክሳውያን ከአሕዛብና ከመናፍቃን የሚለዩት ረቂቁን የሥላሴን ልጅነት ከተቀበሉባት ሰዓት ጀምሮ በአንገታቸው ማዕተብን በማሰራቸው ነው፡፡ይህን በተመለከተ ወይሮ ዘውዴ ገ/ እግዚአብሔር “ማዕተብ ባንገቱ ያሰረ ሰው ስለ ራሱ ሳይናገር ስለርሱ ምንነት በአንገቱ ያሰረው ማዕተብ ይናገርለታል፡፡ነገር ግን አንድ ሰው በአንገቱ ላይ ማዕተብ ካላደረገ ክርስቲያን ይሁን አሕዛብ፣ ኦርቶዶክሳዊ ይሁን መናፍቅ ምን እንደሆነ ቢያንስ ውጫዊ በሆነው ሁኔታ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ስለዚህ ማዕተብ በአንገታችን በማሰር ወልድ ዋሕድ ብለን የምናምን የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ መሆናችንን እንገልጻለን” (፳፻፰ ዓ.ም. ገጽ ፵፱) በማለት ያስረዳሉ፡፡

ሉሌ መልአኩም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በተሰኘ መጽሐፋቸው ማዕተብ በአንገት የማሰርን ሥርዐት በ፮ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ያዕቆብ ዘአልበረዲ እንደሠራና ለምን እንደሠራው ሲገልጹ “የተዋሕዶን እምነት የሚከተሉ ምእመናንንም ከመናፍቃን ለመለየት ተከታዮቹ የሆኑ ምእመናን በአንገታቸው ማዕተብ እንዲያስሩ ሕግ የሠራ እሱ ነው” (፲፱፹፮ ዓም. ገጽ ፲፵፯) በማለት አስረድተዋል፡፡ስለዚህ የማተብ አስፈላጊነቱ ምንድን ነው ከተባለ አንዱ አማኞች ከአሕዛብና ከመናፍቃን ተለይተን የምንታወቅበት መለያ ማለት ነው፡፡

**ለ. የአባቶቻችንን ሥርዐት እናስጠብቅበታለን፦** ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን በርከት ያሉ መገለጫዎች አሏት፡፡አንድ አማኝ ሃይማኖቱን የሚገልጸው በምግባር ነው፡፡በአማኞች ልቡና ታትማ የምትኖረው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትም የምትገለጸው በሥርዐት ነው፡፡ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን ከምታስተምራቸው በርካታ ሥርዐቶች መካከል አንዱ ማንኛውም አማኝ በስመ ሥላሴ ከተጠመቀበት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ የማይፈታ ማዕተብ በአንገቱ ላይ ማሰር ነው፡፡ይህን ሥርዐት አባቶቻችን እግዚአብሔር በገለጸላቸው መንገድ ሠርተውልናል፡፡ይህ የአባቶች ሥርዐት ደግሞ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን እንደ መንፈሳዊ አባትነቱ ሁሉንም ልጆ እያለ ይመክራል፡፡በምሳሌውም “ልጄ ሆይ የአባትህን ሕጎች ጠብቅ፤ የእናትህንም ትእዛዝ ቸል አትበል፤ ሁልጊዜ በልብህ አኑረው፤ በአንገትህም እሰረው፡፡ስትሄድም ይመራሃል፤ ከአንተም ጋር ይኖር ዘንድ ውሰደው፡፡ስትተኛ ይጠብቅሃል፤ ስትነሣም ያነጋግርሃል” (ምሳ. ፮፥፳-፳፪ በማለት ይህን አባቶቻችን የሠሩልንን ሥርዐት ጠብቀን መኖር እንዳለብን ያስረዳል፡፡ስለዚህ የአባቶቻችንን ሥርዐት የምንጠብቀው ደግሞ በተግባር በመፈጸም ነውና መንፈሳዊውን ልደት ከተወለድንባት ዕለት ጀምሪን በአንገታችን አስረነው እንኖራለን፡፡በዚህም ከአባቶቻችን የወረስነውን ሥርዐት አክብረን እነርሱ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን ክብርና ጸጋም እናገኝበታለን፡፡

**፫. ቢቀር የሚያስከትለውን ውጤት መረዳት**

ከላይ የማዕተብን ምንነትና አስፈላጊነት ተመልክተናል፡፡ለምን ያስፈልጋል የሚለውን በአግባቡ ከተረዳነው ቢቀር ከላይ በአስፈላጊነቱ የተጠቀሱትን ሁሉ እናጣለን፡፡ሰው ማንነቱን አጥቶ የሚኖረው ኑሮ ኑሮ ሊባል አይችልም፡፡ወይዘሮ ዘውዴ ገብረ እግዚአብሔር ከላይም በተጠቀሰው ማዕተብና ክርስትና በተሰኘ መጽሐፋቸው “ማዕተብ ከክርና ከጨርቅ በላይ የክርስትና እምነት ወካይ ስለሆነ ማዕተብ መበጠስ ማለት ክርስቶስን መካድ ማለት ነው፡፡ጥንቱንም ማዕተቡ የታሰረው ለጌጥ ሳይሆን ክርስቲያንነትን ለመግለጥ ዓርማ ተደርጎ ነውና” (፳፻፰ ዓ.ም. ገጽ፸፱) በማለት ማዕተብ የሚታሰረው ክርስትናን ለመግለጥ፣ የክርስቶስ ተከታይ መሆናችንን በተግባር ለመመስከር ነውና ማዕተብ መፍታት ማለት ማንነትን ማጣት፣ ብሎም ሃይማኖትን እንደመካድ ይቆጠራል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ዛሬ ዛሬ ክርስትናውን በስም እንጂ በተግባር እየኖርነው አይደለም፡፡ክርስትና ደግሞ በልብ የሚያምኑት፣ በአንደበት የሚመሰክሩት በተግባር የሚኖሩት ነው፡፡የማዕተቡንም ሆነ የመስቀሉን ምንነትና አስፈላጊነት ኃይል በልብ የምናምነው በአንደበት የምንመሰክረው በተግባር የምንገልጠው መሆን አለበት፡፡ሰዎቹ ክርስትናውን በስም ይኖሩታል በተግባር ግን ሲገልጡት አይስተዋልም፡፡

ምን አልባትም አንዳንዶች ለምን ማዕተብ እንደማያስሩ ሲጠየቁ የሚመልሱት ምላሽ ከሰው ጋር ስሆን ስለሚያስተቸኝ፣ ለጓደኞቼ ደስ ይበላቸው ብየ ወዘተ. . . የሚሉ ደካማ ምክንያቶችን ይሰነዝራሉ። ይህ ደግሞ ማንነትን መጥላት፣ በራስ አለመተማመን፣ ከሰማያዊውና ከዘለዓለማዊው ክብርና ደስታ ይልቅ ለጊዜያዊው ትችት ቦታ መስጠት ብሎም የምናምነውን ሃይማኖት በአግባቡ ካለመረዳት የሚመጣ ነው።

## መፍትሔ

ውድ እኅታችን ወለተ ወልድ ቤተ ክርስቲያን ከምንችለው በላይ ተጨንቀን እንድንኖር አታዝዘንም።ልንደራደርበት የማይገባን እግዚአብሔርን ካዱ፣ ለጣዖት ስገዱ የሚለን ከመጣ ብቻ ነው። ይህን ደግሞ ከሠለስቱ ደቂቅ ሕይወት መማር እንችላለን።

ንጉሡ ላቆመው ጣዖት ስገዱ ሲባሉ "ናቡከደነፆር ሆይ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አንፈልግም" (ዳን.፫፥፲፮) በማለት ቁርጠኝነታቸውን አሳውቀዋል።ሥርዐትን በተመለከተ ግን በእኛ ፈቃድ የምንሽረውና የምናጸድቀው አይደለም እንጂ ከአባቶቻችን ጋር እየተመካከርን እንደሁኔታው ልናከናውነው እንችላለን።ስለዚህ መፍትሔ ይሆናሉ ያልናቸውን እንደሚከተለው እንጠቁማለን።

### ሀ. ጥበብ መንፈሳዊን መጠቀም

በቀድሞ ግብሩ አሳዳጅ የነበረው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለአገልግሎት ሲል መሆን የሌለበትን ሁሉ እየሆነ ሕዝቡን ወደ ቀናች ሃይማኖት መልሷል። ይህንም ተግባሩን ሲገልጥ "እኔ ከሁሉ ይልቅ ነጻ ስሆን ብዙዎችን ወደ ሃይማኖት እሰበስባቸው ዘንድ እንደ ባሪያ ራሴን ለሁሉ አስገዛሁ። አይሁድን እጠቅማቸው ዘንድ ለአይሁድ እንደ አይሁዳዊ ሆንሁላቸው፤ ከኦሪት በታች ያሉትን እጠቅም ዘንድ እኔ ራሴ ከኦሪት በታች ሳልሆን ከኦሪት በታች እንዳለ ሰው ሆንሁላቸው። የእግዚአብሔርን ሕግ የዘነጋሁ ሳልሆን በክርስቶስ ሕግም ሳለሁ ሕግ የሌላቸውን እጠቅማቸው ዘንድ ሕግ ለሌላቸው ሕግ እንደሌለው ሆንሁላቸው" (፩ቆሮ.፱፥፲፱-፳፩) በማለት አስረድቶናል። ስለዚህ የሐዋርያውን የቅዱስ ጳውሎስን ሕይወት አብነት አድርገን በእርሱ ተግባር መንቀሳቀስ ያስፈልገናል።

የቤተ ክርስቲያን መተርጒማን እንደሚያስረዱን በአንድ ወቅት ልብሰ ጣዖት ለብሶ ካህነ ጣዖት መስሎ ለሕዝቡ ሐዋርያትን የሚተችና የሚያሳድድ መስሎ ግን ወደ እግዚአብሔር ተገቢውን ጸሎት በማድረጉ ሙት አስነሥቶ በርካታ ሕዝብ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ እንደመለሰ ይነገራል። ስለዚህ ማዕተብ አያስፈልግም በሚል ስሜት ሳይሆን መሠረታዊ ሥራ መሥራት እስከሚቻል የሐዋርያውን የቅዱስ ጳውሎስን ጥበብ መጠቀም ይቻላል።ይህ ሲባል ግን እስከ መጨረሻው መዘናጋት እንዳይኖርና ከበረከት ውጪ ላለመሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ቅዱስ ጳውሎስ ሥራ መሥራት ባለበት ወቅት ሊሆን የማይገባውን ሆኗል።እኛም ከንቱና ደካማ በሆነ ምክንያት ሳይሆን ሥራ ልንሠራ በሚገባን ወቅት የቅዱስ ጳውሎስን ጥበብ ብንጠቀም ለእኛም ሆነ ለሌላው እንጠቅማለን እንጂ አንጎዳም። ከዚህ ባለፈ ግን ዘመኑ ባመጣው ከንቱ ሥልጣኔ፣ ሊጎዳን ካልሆነ በቀር ሊጠቅመን በማይችል ትችትና ይሉኝታ ከእኛ የሚጠበቀውን ባናደርግ እንቀጣበታለን። ይልቁንም ለጓደኞቻችን አርአያ ልንሆንበት የሚገባውን ተግባር ባለመፈጸማችን እንጠየቅበታለን።

### ለ. በቅርብ ከሚኖሩ መንፈሳውያን አባቶች ጋር በመመካከር እንደሁኔታው ማድረግ።

ከላይም ለመጠቆም እንደተሞከረው ካህናት አባቶች ትምህርተ ሃይማኖትን ማለትም በምሥጢረ ሥላሴ፣ በምሥጢረ ሥጋዌ፣ በምሥጢረ ጥምቀት፣ በምሥጢረ ቍርባን በምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ወዘተ. ባሉት ላይ ካልሆነ በቀር እንደሁኔታው እየተመለከቱ በአጽንዖትና በአቅልሎት መበየን ይችላሉ። የሥላሴን አንድነት ሦስትነት አነሰ ብለው ወደ አራት በዛ ብለው ወደ ሁለት መቀየር አይቻልም። ያለምሥጢረ ጥምቀትና ቍርባን ልጅነትን ማሰጠት ብሎም ወደ መንግሥተ ሰማያት ማስገባት አይቻልም። ሥርዐትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ግን እግዚአብሔር በገለጸላቸው መጠን እንደ ሁኔታው ማሻሻልና ምእመናን እንዲገለገሉበት ማድረግ ይችላሉ።

በአጠቃላይ እኅታችን ወለተ ወልድ አንቺ የተቸገርሽበት ጉዳይ ምን አልባት ቀድሞ መታየት ያለበትን ነገር ማየት አለመቻልሽ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ከሆነ በኋላ በማይመለስ ነገር መነጋገሩ ጥቅም የለውምና ሊሆን የሚችለውን ነገር ማሰቡ የግድ ይላል። ከዚህም አልፎ አንቺን ያስጨነቀሽ ነገር ማዕተብ የመፍታት የአለመፍታት ሁኔታ እንጂ ከማያምን ሰው ጋር መኖርን ለምደሽው እንደችግር አልተመለከትሽው ሊሆን ይችላል።ስለዚህ ማሰብና መፍትሔ መፈለግ የሚኖርብሽ ደግሞ በእነዚህ ሁሉ ስለሆነ ዛሬ ማዕተብ በማድረግና ባለማድረግ ብቻ ሳይሆን ባለቤትሽን በማስተማርና በማሳመን ወደተቀደሰችው ሃይማኖት መመለስ ያስፈልጋልና በዚህ ልክ ጥረት ማድረግ ይኖርብሻል። እስከዚያው ግን ከላይም እንደተገለጸው እግዚአብሔር የፈቀደልሽን መልካም ሥራ እስክትሠሪ ድረስ መተው የምትችይ መሆኑን እና አለመሆኑን በቅርብሽ ካሉ አባቶች ቀረብ ብለሽ ብትመካከሪ የተሻለ መፍትሔ ታገኛለሽ የሚል ጥቆማ እንሰጥሻለን።